# ምዕራፍ አንድ

## መግቢያ

### 1.1 የጥናቱ ዳራ

ግርሐምና ፔሪን (2007፡3) ‹‹ጥሩ መጻፍ ለታዳጊዎች አማራጭ ብቻ ሳይሆን አስፈላጊ ነገርም ነው፡፡ አንብቦ እንደመረዳት ሁሉ የመጻፍ ክሂልም የትምህርታዊ ስኬት አመላካች ነው፡፡ በማህበራዊ ህይወትና በአለም አቀፍ ኢኮኖሚ ውስጥ ለመሳተፍ እንደ መሠረታዊ ቅድመ ሁኔታ ነው›› በማለት ስለመጻፍ ጠቀሜታ ይመክራሉ፡፡

ከቋንቋ ትምህርት አንዱ ግብ ተማሪዎችን በመጻፍ ጥሩ ደረጃ ላይ ማድረስ ነው፡፡ እውነታው ግን የአብዛኛው ተማሪ ምሬት ከአመታት የቋንቋ ትምህርት ቡኋላ የመጻፍ ችግር አሁንም የሚገጥማቸው መሆኑን ነው፡፡ በእርግጠኝነትም መምህራን እነዚህን ችግሮች ሊገነዘቡ ይገባል፡፡ ይሁንና እነዚህን ችግሮችን ለማስወገድ መጻፍን ስኬታማ በሆነ ዘዴ በማስተማር በአንድም ሆነ በሌላ ምክንያት ሊያሳኩ እንዳልቻሉ ብሩክስና ግራውንድይ (1990) ይገልጻሉ፡፡ መጻፍን ተማሪዎች የሚሳተፉበት፣ የሚደሰቱበት፣ የማይጨነቁበትና ጎበዝ የሚሆኑበት ሂደት አንጻር ልንመለከተው ይገባል፡፡ ከዚህ አንጻር መምህሩ መጻፍን መልእክት ማስተላለፊያ ብቻ ሳይሆን መልእክት የሚያድግበትና የሚጎለብትበት መሆኑን ሊያስብ እንደሚገባ ብራዎን(2001፡337) ይገልጻሉ፡፡

እንደ ብየርኒ (1988፡4) የመጻፍ ችግሮችን በዋናነት በሦስት ከፍለዋል፡፡ እነዚህም ስነልቦናዊ፣ ስነልሳናዊና አዕምሯዊ እንደሆኑ ይገልጻሉ፡፡ እነዚህም ችግሮች ተማሪዎች በመጻፍ ስኬታማ ሊያደርጉ የማይችሉ ናቸው፡፡ በመሆኑም መምህሩ ለእነዚህ ተጽእኖዎች ትኩረት ሊሰጥና ተማሪዎችን በመርዳት ከፍተኛ ሚና ሊጫወት የሚችለውን የመጻፍ ማስተማሪያ ዘዴን ሊረዳ ይገባል፡፡

የዚህ ጥናትም አላማ ቁጥጥር፣ መር፣ ነጻ እና ሂደታዊ የመጻፍ ማስተማሪያ ዘዴዎች የመጻፍ ትምህርትን በማጎልበት ረገድ ያላቸውን ሚና መተንተን ነው፡፡ ዘዴዎቹም ተማሪዎችን በመጻፍ ምን ያህል ያሳትፋሉ? ተማሪዎችን በመጻፍ ምን ያህል ያጎብዛሉ? ተማሪዎችን በመጻፍ ምን ያህል ያስደስታሉ? በተማሪዎች ላይ ምን አይነት የመጻፍ ጭንቀትን ምን ያህል ይቀንሳሉ? የሚሉትን ጥያቄዎች መተንተን የጥናቱ አቢይ ጉዳይ

ነው፡፡ ጥናቱም በአምቡዬ ሁለተኛ ደረጃ ኦሮመኛ አፈ-ፈት የሆኑ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎችን ተተኳሪ በማድረግ ተካሂዷል፡

## 1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

ብየርኒ(1988፡4) የተማሪዎችን መጻፍ ከሚያከብዱት ችግሮች ጭንቀትና ተነሳሽነት፣ በራስ የመኩራት እጦትና በራስ የመተማመን ጉድለት እንደሆኑ በመግለጽ ተጽእኖ ተኮር መፍትሄ በመስጠት ሊወገዱ እንደሚችሉ ይገልጻሉ፡፡ ይህም በአጠቃላይ የመማር ሒደቱ ላይ አጽንኦት መስጠትን ይመለከታል፡፡ በመሆኑም ተማሪዎችን ለጥሩ ጽሁፍ የሚያበቁ አስፈላጊ ክሂሎችን እንዲይዙ መርዳት ብቻ ሳይሆን የመጻፍ ትምህርት የሚሰጣቸውን እድል በመጠቀም ስለራሳቸውና ስለአለም የተሻለ እንዲረዱ ማድረግም ጭምር እንደሆነ ይመክራሉ፡፡ በተመሳሰይም ይህንን ጉዳይ አስመልክቶ ዊሊያም(1985፡38) "መምህሩና የመማሪያ መጻህፍት አዘጋጆች ወቅታዊ ስነልቦናዎችን እንደ መርህ መከተል ይኖርባቸዋል" በማለት ይመክራሉ፡፡

በአምቡዬ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለቋንቋ መምህራን የቀረበው የቅድመ ጥናት መጠይቅ ውጤት እንደሚያመለክተውም በመጻፍ ትምህርት የተማሪዎች የመጻፍ ችሎታ ዝቅተኛ እንደሆነ ነው፡፡ በጣም ጥቂት ተማሪዎች ብቻ ናቸው ደህና የሚባል የመጻፍ ችሎታ ደረጃ ላይ ያሉት፡ ለተማሪዎች የመጻፍ ችሎታ መቀነስ መንስኤዎቹ የተለያዩና ብዙም ናቸው፡፡ ምናልባትም ችግሩ የመነጨው የመጻፍ ትምህርትን የምናስተምርባቸው የመጻፍ ማስተማሪያ ዘዴዎች የተማሪዎችን ጭንቀት በመቀነስ፣ ተሳትፏቸውን በመጨመርና መጻፍን አስደሳች ተግባር በማድረግና የመጻፍ ጉብዝናቸውን በማጎልበት ያላቸውን ሚና ባለመረዳትና ለይቶ ባለመጠቀም አንጻር ሊሆን ይችላል፡፡

ስለመጻፍ መጻፍ ትምህርት ስናነሳ መምህራን የሚያነሱት ምክንያት በቂ ሰአት ያለመኖር፣ የተማሪዎች ብዛት፣ ምቹ መቀመጫ ያለመኖር፣ የተማሪዎች ፍላጎት እንደ እንቅፋት ያነሳሉ፡፡ ሌሎች ደግሞ ጥሩ የሆነውን የማስተማሪያ ዘዴን ለይቶ ያለመገንዘብና ለተማሪዎች ለመጠቀም ይሰላቻሉ፡፡ ይህም ምናልባት ስኬታማ የሆነውን የመጻፍ ማስተማሪያ ዘዴን ሚና ያለመገንዘብና የተማሪዎችን የመጻፍ አፈጻጸምን ከፍ የሚያድርግ የስሜት ፍላጎትን ለመፍጠር መሰላቸታቸው ነው፡፡

## 1.3 የጥናቱ መሪ ጥያቄዎች

የመጻፍ ትምህርትን በማጎልበት መምህራንና ተማሪዎች በውዴታ ሊያገባቸው የሚችል ቀዳሚ ግብ ነው፡፡ በተለይም የመጻፍ ችግር ያለባቸውን ተማሪዎችን በማብቃት ረገድ፡፡ ይህ ጥናትም በዋናነት በመር፣ በቁጥጥር፣ በነጻና በሒደታዊ የመጻፍ ማስተማሪያ ዘዴዎች የመጻፍ ትምህርተን በማጎልበት ረገድ ያለቸው ሚና ምንድ ነው? የሚለውን መሪ ጥያቄ ታላሚ አድርጎ የተነተነ ሲሆን የሚከተሉትን ንዑሳን ጥያቄዎችን መልሷል ተብሎ ይገመታል፡፡

- መር፣ ቁጥጥር፣ ነጻ እና ሒደታዊ የመጻፍ ማስተማሪያ ዘዴዎች በመጻፍ ትምህርት ተሳትፎ ላይ ምን አንድምታ አላቸው?
- መር፣ ቁጥጥር፣ ነጻና ሒደታዊ የመጻፍ ማስተማሪያ ዘዴዎች በመጻፍ ትምህርት የመጻፍ ጉብዝናን በማሻሻል ረገድ ምን ይመስላሉ?
- መር፣ ቁጥጥር፣ ነጻና ሒደታዊ የመጻፍ ማስተማሪያ ዘዴዎች በመጻፍ ትምህርት መጻፍን አስደሳች ተግባ ከማድረጋቸው አንጻር ያላቸው ሚና ምንድ ነው?
- መር፣ ቁጥጥር፣ ነጻና ሒደታዊ የመጻፍ ማስተማሪያ ዘዴዎች በመጻፍ ትምህርት ጊዜ የመጻፍ ጭንቀት ከመቀነስ አንጻር ምን አይነት ሚና አላቸው? የሚሉት ጥያቄዎች በዚህ ጥናት ውስጥ ተመልሰዋል ብሎ አጥኚው ይገምታል ፡፡

በእነዚህ የጥናቱ ጥያቄዎች መነጽርነት መላምቱም የሚከተለውን ይናገራል፡፡

- መር፣ ቁጥጥር፣ ነጻ እና ሒደታዊ የመጻፍ ማስተማሪያ ዘዴዎች የመጻፍ ትምህርት ተሳትፎን ይጨምራሉ፡፡
- መር፣ ቁጥጥር፣ ነጻና ሒደታዊ የመጻፍ ማስተማሪያ ዘዴዎች በመጻፍ ትምህርት በመጻፍ ጎበዝ ያደርጋሉ፡፡
- መር፣ ቁጥጥር፣ ነጻና ሒደታዊ የመጻፍ ማስተማሪያ ዘዴዎች በመጻፍ ትምህርት ጊዜ የመጻፍ ተግባርን አስደሳች ያደርጋሉ፡፡
- መር፣ ቁጥጥር፣ ነጻና ሒደታዊ የመጻፍ ማስተማሪያ ዘዴዎች በመጻፍ ትምህርት ጊዜ የመጻፍ ጭንቀትን ይቀንሳሉ፡፡

## 1.4 የጥናቱ አላማ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ መር፣ ቁጥጥር፣ ነጻና ሒደታዊ የመጻፍ ማስተማሪያ ዘዴዎች የመጻፍ ትምህርትን በማጎልበት ረገድ ያላቸውን ሚና በመመልከት መተንተን ነው፡፡ የሚከተሉትን ንኡሳን አላማዎችን ሊያሳካ ይችላል፡፡

- መር፣ ቁጥጥር፣ ነጻ እና ሒደታዊ የመጻፍ ማስተማሪያ ዘዴዎች የመጻፍ ትምህርት ተሳትፎ ላይ ያላቸውን አንድምታ መግለጽ፡፡
- መር፣ ቁጥጥር፣ ነጻና ሒደታዊ የመጻፍ ማስተማሪያ ዘዴዎች በመጻፍ ትምህርት ጊዜ በመጻፍ ጎበዝ በማድረግ ያላቸውን አዎንታዊ ወይም አሉታዊ አስተዋጽኦ ማሳየት፡፡
- መር፣ ቁጥጥር፣ ነጻና ሒደታዊ የመጻፍ ማስተማሪያ ዘዴዎች በመጻፍ ትምህርት የመጻፍ ተግባርን አስደሳች ከማድረግ አንጻር ያላቸውን ሚና መግለጽ፡፡
- በመር፣ በቁጥጥር፣ በነጻና በሒደታዊ የመጻፍ ማስተማሪያ ዘዴዎች በመጻፍ ትምህርት ላይ የሚያሳድሩትን የጭንቀት ተጽእኖ መለየት፡፡

## 1.5 የጥናቱ አስፈላጊነት

ይህ ጥናት ውጤታማነቱ ከተረጋገጠ ንድፈ ሐሳባዊና ተግባራዊ ጠቀሜታዎች ይኖሩታል ብሎ ይታመናል፡፡

### ንድፈ ሐሳባዊ ጠቀሜታዎቹን በተመለከተ

- የዚህ ጥናት ውጤት የመጻፍ ትምህርትን ይበልጥ አዎንታዊ ተዛምዶ ባለው ማስተማሪያ ዘዴ ማስተማር የተማሪዎችን መጻፍ በማጎልበት ጠቃሚ ግብአት ይሆናል ተብሎ ይገመታል፡፡

### ተግባራዊ ጠቀሜታውን በተመለከተ

- ተማሪዎችን ከመጻፍ ችሎታ ጋር ይበልጥ ተዛምዶ ያለውን የመጻፍ ማስተማሪያ ዘዴ መርጦ በማስተማር የመጻፍ ችሎታቸውን እንዲያዳብሩ በማድረግ ላሉበት ደረጃ የሚመጥናቸው የአጻጻፍ ደረጃ ላይ ያደርሳቸዋል፡፡
- መምህሩም የተሻለውን ዘዴ ተጠቅሞ የተማሪዎቹን መጻፍ ማሻሻል ከቻለ የስራ ስኬታማነትና እርካታ ላይ ሊያደርሰው ይችላል፡፡

- ❖ የቋንቋ መማሪያ መጽሐፍት አዘጋጆችም የመጻፍ ማስተማሪያ ዘዴዎችን መሰረት በማድረግ ተማሪዎችን ለደረጃቸው የሚመጥን የመጻፍ ብቃት ላይ እንዲደርሱ፣ ይበልጥ ውጤታማ የሆነውን ዘዴ በመምረጥ፣ የመማሪያ መጻህፍትን እንዲያዘጋጁ ለማድረግ ያስችላቸዋል፡፡
- ❖ የተማሪውን የመጻፍ ችሎታ በዋናነትና የመናገር ችሎታን በተጓዳኝነት በማዳበር ተማሪውን ለደረጃው የሚመጥን የክህሎት ባለቤት ስለሚያደርግ እንደ ሀገር ወይም እንደ ክልል የተማሪዎችን የአማርኛ ቋንቋ የመጻፍ ክሂልን መቀነስን ተከትሎ በቋንቋ ትምህርት ጥራት ላይ ለሚነሱ ጥያቄዎች መልስ ሊሰጥ ይችላል ተብሎ ይገመታል፡፡
- ❖ ለሌሎች ንጽጽራዊ ጥናቶች መነሻ ሐሳብ ይሆናል፡፡

በአጠቃላይ በዚህ ጥናት መምህራን የመጻፍ ማስተማሪያ ዘዴዎች የመጻፍ ትምህርትን በማጎልበት ያላቸውን ሚና በመረዳት ለመጠቀም እንዲወስኑ ማስቻል ነው፡፡ ነገር ግን ውጤታማውን የማስተማሪያ ዘዴ ለመጠቀም የመጻፍ ማስተማሪያ ዘዴዎች ሒደት በሙሉ መረዳት ላይ ይመሠረታል፡፡

## 1.6 የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት መር፣ ቁጥጥር፣ ነጻና ሒደታዊ የመጻፍ ማስተማሪያ ዘዴዎች የመጻፍ ትምህርትን በማጎልበት ረገድ ያለቸውን ሚና የሚተነትን ነው፡፡ የመጻፍ ማስተማሪያ ዘዴዎች የተለያዩ ሚናዎች ቢኖሯቸውም በዚህ ጥናት ግን የመጻፍ ማስተማሪያ ዘዴዎቹ የመጻፍ ትምህርትን አሳታፊ ከማድረጋቸው አንጻር፣ በመጻፍ ጎበዝ ከማድረጋቸው፣ ጭንቀትን ከመቀነሳቸውና መጻፍን አስደሳች ተግባር ከማድረጋቸው አንጻር ያላቸውን ሚና ተንትኗል፡፡ ጥናቱም ከጅማ ከተማ 56 ኪሎ ሜትር ላይ እርቆ በጅማ ዞን በሊሙ ኮሳ ወረዳ በአምቡዬ ከተማ በሚገኘው በአምቡዬ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ9ኛ ክፍል ኦሮመኛ አፈ-ፈት ተማሪዎች ተተኳሪነት ተካሂዷል፡፡ አጥኝው ይሄንን የጥናቱን አከባቢ በመምረጡ ምክንያት የሚያስተምርበት ቦታ በመሆኑ ጊዜውንና የጥናቱን ወጭ በአገባቡ ለመጠቀም እና የጥናቱን ውጤታማነት ለማረጋገጥ አስችሎታል፡፡

## 1.7 የጥናቱ ውስንነት

በአምቡዬ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የአማረኛ ቋንቋ መምህራን ጋር በተደረገው ቡድን ተኮር ቅድመጥናት ውይይት የመጻፍ ትምህርትን የሚያደናቅፉ ተጽእኖዎች እንዳሉ ተደርሷል፡፡ እነዚህም ተጽእኖዎች የመምህሩን አላማና ውሳኔዎችን ሊጎዱ የሚችሉ ናቸው፡፡ እነዚህም አመራራዊ ቅድመ ሁኔታዎች፣ የመደበኛ ምዘና አዘገጃጀትና ትግበራና የንግድ መማሪያ መጻህፍት አደረጃጀት ናቸው፡፡

የትምህርት ቤቱ አመራር መጻፍን ለማስተማር ያስቀመጠው ምንም አይነት መመሪያ የለም፡፡ የትምህርት ቤቱ አመራር ብቻ ሳይሆን የኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ መጻፍን ለማስተማር ያስቀመጠው ሐላፍትና የለም፡፡ በመሆኑም መደበኛ ልምምዶችን ለማቅረብ በሁለቱም አካላት(በመምህሩና በአመራሩ) መካከል ምንም አይነት ሙግት የለም፡፡ ስለሆነም በትምህርት ቤቱ መጻፍን ለማስተማር የተቀመጠ ሐላፍትናና አላማ ባለመኖሩ የመጻፍ ትምህርት ላይ ተጽእኖ ሊያሳድር ችሏል፡፡

የትምህርት መስኮችና የክፍለ ጊዜ ምደባም በመጻፍ ማስተማር ትግበራ ላይ ተጽእኖ ያሳደሩ ናቸው፡፡ በአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መርሃ ትምህርት ላይ የተቀመጠው የማስተማሪያ የክፍለጊዜ ምደባ በሳምንት ሦስት ክፍለጊዜ ቢመደብም ይህንን እውን የሚያደርግ የክፍለ ጊዜ ምደባ በትምህርት ቤቱ አልተደረገም፡፡ ይህም በትምህርት ቤቱ ለአማርኛ ቋንቋ የተሠጠው የክፍለ ጊዜ ሽፋን በሳምንት አንድ ብቻ ነው፡፡ በመሆኑም ለመጻፍ ተብሎ የሚመደብ ጊዜ የለም፡፡ መምህሩ በራሱ ነው አንዱን ክፍለጊዜ የሚጠቀመው፡፡ በዚህም የቡድን ተኮር ውይይት መምህራኑ በመደበኛነት ለመጻፍ ትምህርት የሚያውሉትን ጊዜ መገመት እንዳልቻሉ ተናግረዋል፡፡

በእነዚህ ጉዳዩች ምክንያት በጥናቱ የመጻፍ ማስተማሪያ ዘዴዎችን ትገበራ ከመደበኛው የማስተማሪያ ክፍለጊዜ ውጭ እንዲከናወን ተገዷል፡፡ ይህ ምናልባትም ጥናቱን ጎደሎ ሊያደርገው ችሏል፡፡ ምክንያቱም የጥናቱን አካሄድ ከተፈጥሯዊው ክንውን ይልቅ በአርቴፊሻል መቼት በመካሄዱ ነው፡፡ ይህም የተወሰኑ ናሙናዎችን በመምረጥ ብቻ የመጻፍ ማስተማሪያ ዘዴዎች እንዲተገበሩ በማድረግ የተማሪዎችንፍጻ በማጎልበት ረገድ የትኛው ዘዴ ከፍተኛ ሚናን እንደተጫወተ ለመመልከት ተሞክሯል፡፡ በዚህ ጥናት

የተገኘው ውጤትም ምናልባት በመደበኛው ክፍል ቢከናወን ውጤቱ የተለየ ሊሆን ይችል ይሆናል፡፡

ሌላው የጥናቱ ውስንነት ምንጭ በትምህርት ቤቱ የመምህራኑ የመጻፍ ማስተማሪያ ዘዴዎች ግንዛቤም አናሳ በመሆኑ ትግበራዎቹ በአጥኚው በራሱ እንዲከናወኑ ተደርገዋል፡፡ ይህ ምናልባት የጥናቱ ውጤት የተሟላ እንዳይሆን አድርጎታል፡፡ ምክንያቱም ከአጥኚው አድሏዊ አመለካከት የጸዳ ሊሆንም ላይሆንም፡፡ ምናልባትም መምህራኑን በስልቶቹ አሰልጥኖ ወደትግበራ በማስገባት ቢከናወን ይህንን ችግር ሊቀርፍ ይችል ይሆናል፡፡ ነገር ግን የአማረኛ ቋንቋ መምህራን ቁጥር ጥቂት በመሆኑ፣ የክፍለ ጊዜ ውስንነት ጥናቱ እንዲወሰን አድርገውታል፡፡ የጥናቱም ውጤት የተሟላ እንዳይሆን ሊገድቡት ችለዋል፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

# የተዛማጅ ድርሳናት ክለሳ

## 2.1 ንድፈ ሐሳባዊ ቅኝት

### 2.1.1 የመጻፍ ትምህርት ማስተማሪያ ዘዴዎች ንድፈ ሐሳባዊ መሠረቶች

ኮነግጁን(2005፥2) ሲልቫ(1990)ን ዋቢ በማድረግ በሁለተኛ ቋንቋ የመጻፍ ትምህርትን ማስተማር ታሪክ ውስጥ በአራት ተጽእኖ ፈጣሪ ስልተ ትወራዎች አማካኝነት በአራት ደረጃዎች ውስጥ አልፏል፡፡ እነዚህም የቁጥጥር ስልተ ትወራ፣ አሁን ተለምዷዊ አሳማኝ ስልተ ትወራ፣ ሒደታዊ ስልተ ትወራና ማህበራዊ ስልተ ትወራ ናቸው፡፡

የመጀመሪያው ደረጃ በቁጥጥር ወይም የመር ስልተ ትወራ ሲሆኑ የመዋቅራዊ ስነልሳንናና የባህራዊያን ስነልቦና ንድፈ ሐሳብ ተጽእኖ አማካኝነት የመጣ ነው፡፡ ይህ ስልተ ትወራ የመጻፍ ትምህርትን የሚመለከተው መጻፍን በመለማመድ የመጻፍ ልማድን መመስረት ነው፡፡ ተማሪዎችም የዐነገር ቅጥንብሮችንና የቃላት ፍችን በመጻፍ አማካኝነት በመለማመድ ይማራሉ፡፡

ሌላው በሁለተኛ ቋንቋ መጻፍን ማስተማር ሁለተኛ ደረጃ የመጣው ሐሳብ በካምፕላንስ ገንቢ አሳማኝ ንድፈ ሐሳብ(Constructive Rhetorical) ተጽእኖ አማካኝነት የተፈጠረው አሁን-ተለምዷዊ ስልተ ትወራ ነው፡፡ በዚህ ስልተ ትወራ ንድፈ ሐሳብ ለመጻፍ መማር አደረጃጀታዊ ቅጥንብሮችን መለየትና ማስረጽን ይመለከታል፡፡

በሦስተኛነት የተቀመጠው የሁለተኛ ቋንቋ መጻፍን ማስተማር ሦስተኛ ደረጃ ሒደታዊ ስልተ ትወራ ነው፡፡ ይህ ስልተ ትወራ በአዕምሯዊ እድገት ንድፈ ሐሳብ (Conginative Developmental Theories) ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ በዚህም ስልተ ትወራ መጻፍን መማር ማለት ስኬታማና ብቃት ያላቸውን የመጻፍ ዘዴዎችን ማጎልበት ማለት ነው፡፡

አራተኛው የሁለተኛ ቋንቋ መጻፍ ማስተማሪያ ስልት ትወራ ማህበራዊ ስልተ ትወራ ነው፡፡ በዚህም ስልተ ትወራ መጻፍን መማር በአቅርቦተ ሐሳብ ማህበረሰብ ውስጥ ማህበራዊ የመሆን አካል ነው፡፡ ማለትም ምን እንደሚጠበቅና ለመገመት የመሞከር ግኝት ነው፡፡

በአጠቃላይ እንደ ኮንግ ጁን(2005፡2) የሁለተኛ ቋንቋ መጻፍን ማስተማሪያ ስልተ ትወራዎች በዋናነት በአራት ንድፈ ሐሳቦች የተደገፉ ናቸው፡፡ እነሱም ተቃርኗዊ አሳማኝ ንድፈ ሐሳብ፣ አዕምሯዊ እድገት ንድፈ ሐሳብ፣ ተግባቦታዊ ንድፈ ሐሳብና የህብረተሰብ ግንባታ ንድፈ ሐሳብ ናቸው፡፡ ከእነዚህም ተቃርኗዊ አሳማኝ ንድፈ ሐሳብ፣ አዕምሯዊ እድገት ንድፈ ሐሳብና ህብረተሰብ ግንባታ ንድፈ ሐሳብ ከአሁን አሳማኝ ስልተ ትወራ፣ ሒደታዊ ስልተ ትወራና ማህበራዊ የሁለተኛ ቋንቋ ማስተማሪያ ስልተ ትወራዎች ጋር በተከታታይ የተደጋገፉ ናቸው፡፡ በተጨማሪም የቁጥጥርና የመር ስልተ ትወራዎች በመዋቅራዊ ስነ ልሳንና በባህራውያን ስነልቦና የተደገፉ ናቸው፡፡ ተግባቦታዊ ንድፈ ሐሳብ ተጽእኖ አሳዳሪነት የተፈጠረ መሆኑን ኮነግ ጁን(2005፡3) በመግለጽ ተግባቦታዊ ንድፈ ሐሳብ በተግባቦታዊ ባህሪው በአራቱም የመጻፍ ስልተ ትወራዎች ውስጥ የሚንጸባረቅ መሆኑን ይገልጻል፡፡ በመሆኑም እነዚህ ንድፈ ሐሳቦች ከሁለተኛ ቋንቋ መጻፍ ማስተማሪያ ስልተ ትወራዎች ጋር ከመቆራኘታቸውም በላይ ለመጻፍ ማስተማሪያ ዘዴዎች ንድፈ ሐሳባዊ ፍሬምዎርክ መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡ በማስከተልም ኮነግ ጁን(2005፡8) የአርደን(1987)፣ ቪክቶሪ(1995)ና ሳሳንኪ(2000) የመጻፍ ማስተማሪያ ዘዴዎች አከፋፈል በንድፈ ሐሳቦች ላይ ያልተመሰረቱ በመሆናቸው ከላይ በተጠቀሱት የመጻፍ ማስተማሪያ ንድፈ ሐሳቦች ላይ በመመስረት ኮነግ ጁን(2005፡8) የአርደን(1987)፣ ቪክቶሪ(1995)ና ሳሳንኪ(2000) የተዘረዘሩትን 30 የመጻፍ ማስተማሪያ ዘዴዎች ክንውኖችን እንደየ ንድፈሐሳባዊ መሠረታቸው ከፍለዋል፡፡

### 2.1.2 የመጻፍ ትምህርት ችግሮች

መጻፍ ለብዙ ሰዎች ከባድ ተግባር ነው፡፡ ሒልቶንና ሐይደር(1992፡7) ‹‹በርካታ ሰዎች መጻፍን አሰልቺ ተግባር ነው ይሉታል፡፡ በተጨማሪም መጻፍ የትጉህን ስራ ነው ይሉታል›› በማለት ይገልጻሉ፡፡ ብይርኒ(1988፡1) ‹‹ባለሙያ ወይም ባለሙያ ያልሆኑ ሰዎች መጻፍ ቀላል ወይም በድንገት የሚከሰት ክንውን እንዳልሆነ ይስማማሉ፡፡›› በማት ሲገልጹ ፍሪማንና ሪቻርደስ(1996፡101) ዳልይ(1985)ን በመጥቀስ ‹መጻፍ የመማር ሒደት አካልና ለተማሪዎች የሚከብድ፣ የማያሸልምና ለተወሰኑት ተማሪዎች ደግሞ እንደቅጣት የሚቆጠር ተግባር ነው፡፡› በማለት ይገልጻሉ፡፡

ሌላው ጉዳይ ስኩነን(2003፡166) ‹‹የመጻፍ ትምህርት ከአፈፊቱ ይልቅ ለኢ. አፈፊቱ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ ምክንያቱም ኢ. አፈፊቱ ከአፈፊቱ ይልቅ በጥቂቱ የጎለበተ አቅም ብቻ ነው ያለው፡፡›› በማለት ይገልጻሉ፡፡

ብይርኒ(1988፡4) መጻፍን ሊያከብዱ የሚችሉ ችግሮችን በሦስት በመክፈል ዘርዝረዋል፡፡ የመጀመሪያው ስነልቦናዊ ችግር ነው፡፡ ‹‹ስለመስተጋብርና ምጋቤ ምላሽ አስፈላጊነት ሲገልጽ መጨረሻ ላይ ሊቀመጡ የሚችሉ መሆናቸው ነው፡፡ እውነታው መጻፍ ያለብን በራሳችን ነው፤ ካለምንም መስተጋብርና ምጋቤ ምላሽ፡፡ እነሱ በራሳቸው የመጻፍን ተግባር የሚያከብዱ ናቸው፡፡›› በማለት ይገልጻሉ፡፡ ሁለተኛው ችግር ሥነልሳናዊ ነው፡፡ ‹‹ሁሌም እንደሚባለው መናገር የተለያዩ ገጽታዎች አሉት፡፡ መጻፍ ውስጥ ግን ሁኔታዎች የተለያዩ ናቸው፡፡ ረዳት መገለጫዎች በሌሉበት ለቃላት ምርጫ፣ ለቃላት ፊደል ቅርጽ፣ ለመዋቅሮችና ለመሳሰሉት ትኩረት በመስጠት የምንጽፈው ጽሁፍ በቀላሉ መልእክት እንዲተላለፍ ያደርጉታል፡፡›› በማለት ይገልጻሉ፡፡ ሦስተኛው ችግር አዕምሯዊ ነው፡፡ ‹‹ይህም ሐሳብን የማደራጀት ችግርን ነው፡፡ በዚህም ጸሐፊው አንባበቢው በሌለበትና አንባቢውን በማያይበት የሚጽፈው ጽሁፍ በመሆኑ ሐሳቡን በተደራጀ ሁኔታ ሊያስተላልፍ ይገባል፡፡›› እንደ ብይረኒ(1988፡5) ሌላው ተጨማሪ ችግር መጻፍ በራሱ በተማሪዎች ላይ የሚያሳድረው ተጽኖ ነው፡፡ እዚህ ጋር ችግሩ ስነልቦናዊም አዕምሯዊም ነው፡፡ ፍሪማንና ሪቻርደስ(1996፡101) ዊነር(1992)ን በመጥቀስ ተማሪዎች በመጻፍ ላይ ያላቸው አመለካከት በሚል የተጠና ጥናት‹‹የመጻፍ ስጋት በተደጋጋሚ የተለየ አንዱ ችግር ነው፡፡››

ቋንቋ ተማሪዎች ፍላጎታቸውንና ስሜቶቻቸውን ካላካተቱበት ነጻ ስርአት አይደለም፡፡ እንደ ብራዎን(2000፡144) ስለቋንቋ ምንነት ሲያብራራ

> *ቋንቋ ባህሪ ነው፡፡የሰዎች ክንውን አካልም ነው፡፡ ልናክመው የማንችለው ነው፡፡ ከቃላዊ የሰው ልጅ ክንውኖች በመዋቅሩ የተለየ ነው፡፡ የሰው ልጅ ክንውኖች አጠቃላይ መዋቅርን ያቀፈ ነው፡፡ ወደተለያዩ አካላትና ደረጃዎች የሚከፈልም ነው፡፡ ይህም በባህሪ፣ በይዘቱና በአደረጃጀቱ አንጻር ሊታይ ይችላል፡፡*

ይህ የቋንቋ ብያኔ በሁለተኛ ቋንቋ የመጻፍ ትምህርት ላይ ሌሎች ችግሮችም ተጽእኖ ሊያሳድሩ እንደሚችሉ መረዳት ይቻላል፡፡ እንደ አርኖልድና ብራዎን(1999፡8) የተለያዩ ስሜቶች ቋንቋን መማር ላይ ተጽእኖ እንደሚያሳድሩ ይገልጻሉ፡፡ እነዚህም ተጽእኖዎች የተጣመሩና የተዛመዱ ሲሆኑ የአንዳቸውን ተጽእኖ ከሌላኛው ለመነጠል እንደሚያዳግት

ይገልጻሉ፡፡ የስሜት ርስቶች(Affective Domains) ከሚያጠቃልላቸው ነገሮች ጭምር በቋንቋ መማር ላይ የሚያሳድረው ተጽእኖ ለመረዳት የተሻለ ምርመራ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ እነዚህም ጭንቀት፣ ተነሳሽነት፣ በራስ መኩራትና በራስ መተማመን ተጠቃሽ ናቸው፡፡

### 2.1.2.1 ጭንቀት

እንደ ውልፎልክ(2004፡365) ‹‹ጭንቀት እራስን የማስደበርና የመጨናነቅ ስሜት ነው፡፡›› እንደ ኦክስፎርድ(1990) ‹‹ጭንቀት ወቅታዊ ወይም ነባራዊ ሊሆን ይችላል፡፡›› ሁኔታዊ ጭንቀት ተማሪዎች አንድን የተሰጣቸውን ተግባር ለማከናወን ሲፈሩ በቋንቋ መማር ውስጥ ሊከሰት የሚችል ነው፡፡ አልፎ አልፎ ጭንቀት ግለሰባዊ በሽታም ይሆናል፡፡ ይህ ሲሆን ነባሪያዊ ጭንቀት ይባላል፡፡ ብራዎን(2000፡336) በመጻፍ ጊዜ ጭንቀት ሊኖር እንደሚችል ትኩረት ሰጥቶ ሲገልጽ ‹‹የክፍል ውስጥ ድርሰት ጽፈህ መምህሩ ሲጻኝህና ያለምንም የማስተካከያ እድል ደረጃ ሲሰጥህ የተወሰነ ጭንቀት ይሰማሀል፡፡›› በማለት ይገልጻል፡፡

እንደ ስላቪን(2003) ጭንቀት በትምህርት አለም ሊኖር እንደሚችል ይገልጻል፡፡ ጥናቶች እንደሚያነለክቱት መጻፍን ጨምሮ በሁለተኛ ቋንቋ ውጤትና በጭንቀት መካከል አሉታዊ ተዛምዶ እንዳለ ነው፡፡ ለምሣሌ ቼንግና እስካለርት(1999)፣ ማክኢንታዬር(1997)፣ ሮድሪጉኤዝና አብሪው(2003)፣ ዮንግ(1991) ይጠቀሳሉ፡፡

ከዚህ እይታ አንጻር ዉልፎልክ(2004፡365) ኮቪንግተንና ኦሜሊች(1987)ን በመጥቀስ ‹‹ተመራማሪዎች በተከታታይ በትምህርት ቤት ውጤትና በጭንቀት ልኬታዎች መካከል አሉታዊ ተዛምዶ እንዳለ ያመለክታሉ፡፡›› በማለት ይገልጻሉ፡፡

ሐርመር (2005) ‹‹የመጻፍ ጭንቀት በመጻፍ ላይ አሉታዊ አስተሳሰብ እንዲኖር በማድረግ አደገኛነቱ የከፋ ነው፡፡›› ይላሉ፡፡ እንደ ኦክስፎርድ(1990) ‹‹ጎጅ ጭንቀት የተማሪዎችን ተሳትፎ በመቀነስና ቋንቋው ላይ ግልጽ ክልከላን በመፍጠር አሉታዊ ተጽእኖ ያሳድራል፡፡››በማለት ያስገነዝባሉ፡፡

ለእንደዚህ አይነት ስሜት መንስኤዎች የተለያዩ ናቸው፡፡ ኑናን(1991) ‹‹ጭንቀት አዲስ ቋንቋን የመማር ቀዳሚ ጉዳይ ነው በማለት ይገልጻል፡፡›› ሐርመር(2005) የተማሪዎች ፍራቻ መንስኤዎችን ሲገልጹ በእጅጉ ዘርዘር ባለ መልኩ ነው፡፡ የመጀመሪያው በአፍ

መፍቻ እንኳን ሳይቀር የመጻፍ ልምምድ ያለማድረግ፡፡ ሁለተኛው የሚሉትን ነገር ማጣት በራሱ ለተማሪዎች እንቅፋት እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡ በመጨረሻም የተወሰኑ ሰዎች በመጻፍ ክንውኖች ደስተኛ አይደሉም በማለት ያስገነዝባሉ፡፡ እንደመፍትሄም ያስቀመጠው መምህራን የተማሪዎቻቸውን የመጻፍ ልምድ ለመገንባት የተማሪዎችን በራስ መተማመናቸውን ሊያሳድጉ ይገባል፡፡ ይህም ምንአልባት ጥሩ የሆነውን የማስተማሪያ ዘዴ በመምረጥ ሊሆን ይችላል፡፡

ፎንታና(1995፡148) ቢግስ(1990)ን ጠቅሰው እንደገለጹት ‹‹ይህ አይነት ስሜት ከጊዜ ጫናና ከተከታታይ ምዘና የሚመነጭ በመምህሩና በተማሪው መካከል የሚፈጠር ነው፡፡›› ፍሪማንና ሮጀርስ(1996፡102) ሊይ(1991) የመጻፍ መምህር ሲሆን ጭንቀት የተወሰኑ ተጽኖዎች ውጤት እንደሆነ ይገልጻል፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ መምህሩ ሰዋስዋዊ ጥራት ላይ ማተኮሩ ተማሪዎች ትክክለኛ ሰዋስዋዊ ዐ.ነገሮችን ካላመነጩ የመጨረሻው ውጤት ጥሩ እንደማይሆን እንዲያስቡ ያደርጋቸዋል፡፡ ይህም ተማሪዎች ስለጽሁፋቸው ጥራት እንዲጨነቁ ስለሚያደርጋቸው ከእያንዳንዱ ዐ.ነገር ቡኋላ እየቆሙና ወደኋላ እየተመለሱ የዐ.ነገሩን የቃላት ፊደል ቅርጽን፣ የቃላት ቅደምተከተሉንና ሥርአተ ነጥቡን ከፈተሹና ካጣሩ ቡኋላ ወደቀጣዩ ዐ.ነገር እንዲሸጋገሩ ያስገድዳቸዋል በማለት ይገልጻሉ፡፡

እንደ ሊይ ሌላው የጭንቀት መንስኤ ተማሪዎች የሚጽፉበት ርዕስ ነው፡፡ እንደሳቸው አገላለጽ ተማሪዎች ያልሳባቸውን ወይም ያልፈለጉት ርዕስ ላይ እንዲጽፉ ሲደረጉ ይጨናነቃሉ፡፡ ስለሆነም ተማሪዎች በፈለጉት ርዕስ ላይ እንዲጽፉ ነጻነት መስጠቱ ቀለል እንዲላቸው ያደርጋል፡፡ ይህንንም አስመልክቶ ከሊይ ተማሪዎች አንዱ ‹መምህራችን የምጽፍበትን ርዕስ እንዲወስንልኝ አልፈልግም› በማለት እንደገለጸ ይናገራሉ፡፡

እንደ ሊይ ሌላው የጭንቀት መንስኤ ለመጻፍ ምቹ የሆነ ሁኔታ ያለመኖር ነው፡፡ ይህም ተማሪዎች ድርሰትን መፍራታቸው ነው፡፡ ምክንያቱም ተማሪዎች ሁሌም ሐሳብ እንዲያመነጩ፣ እንዲያብራሩ፣ እንዲከልሱና አርትኦት እንዲያከናውኑ በተመሳሳይ ጊዜ ይጠየቃሉ፡፡ ሌላው ድርሰትን የሚፈሩበት ምክንያት መምህሩ ነው በቀይ ብእር የሚያነብላቸው፡፡ ማለትም የመምህሩን አሉታዊ ግምገማን የመፍራት ነው፡፡

### 2.1.2.2. ተነሳሽነት

እንደ ስላቪን(2003፡328) ተነሳሽነትን ‹‹የስኬታማ ማስተማር ጠቃሚ ግብአቶች ከሆኑት ነገሮች አንዱ ነው፡፡›› ይሁንና ተነሳሽነትን ለመበየንም ሆነ ምንጮቹን ለመወሰን አስቸጋሪ ነው፡፡ ምክንያቱም የብዙ ተጽእኖዎች ውጤት ነውና፡፡ ከተማሪው የግል ባህሪና አቅም እስከ ወሳኙ የመማር ግብአት፣ መቼትና የመምህሩ ባህሪ ውጤቶች ስብስብ ነው፡፡ እንደ ስላቪን(2003፡329) የተማሪዎችን ተነሳስቶ ለማስቀጠል የመምህራን ሥራ መሆኑን ይገልጻል፡፡

### 2.1.2.3.በራስ ያለመኩራት

ገንቢ ስልተ ትወራዎች ተማሪዎች እራሳቸውን የመማር ሒደቱ ማእከላዊ አንቀሳቃሽ እንደሆኑ የመቁጠር ግንዛቤያቸውን ከፍ ማድረግ ተገቢ ነው፡፡ ምክንያቱም እንደ ዊሊያምስና በርደን(1999፡194) ይህ እሳቤ ተማሪዎቹ አዲስ የመነቃቃት ስሜትና እውቀት የሚያገኙበት መንገድ ነው፡፡ ይህ እሳቤ ተማሪዎች የተለያዩ ተግባራን እንዲወጡ ያደርጋል፡፡ ስለራሳቸው ያላቸው ግንዛቤም በውስብስቡ በራ የመኩራት ትርጉም ስር የወደቀ ነው በማለት በድጋሚ ይገልጻሉ፡፡ እንደ ውልፎልክ(2004፡71) ‹‹በራስ መኩራት ስለራስህ ያለህ ግንዛቤ ስኬታማ ግንኙነት ነው፡፡ ለምሣሌም ስለምትጽፍበት መንገድ ጥሩ ስሜት ሲሰማህ፡፡›› በማለት ይገልጻሉ፡፡

እንደ ፎንታና(1995፡148) ‹‹ከፍተኛ በራስ መኩራት ሊመጣ የሚችለው በተለያዩ መሠረታዊ ምክንያቶች ነው፡፡ እነዚህም የቤተሰብ ትኩረትና ልጆቻቸውን ማበረታታት እና በብዛት መምህሩም ነው፡፡ ይህም መምህሩ በብዛት የተማሪዎወች በራስ መተማመን እንዲያድግ በማገዝ ስለራሳቸው በራሳቸው እንዲኮሩ ሊያደርግ ይገባል›› በማለት ይገልጻሉ፡፡

በድጋሚ ውልፎልክ(2004፡73) በራስ መኩራትን በመማር ውስጥ ያለውን ሚና አስመልክቶ ሁለት ጥያቄዎችን ተጠየቀ፡፡ የመጀመሪያው በራስ መኩራት በትምህርት ቤት ውስጥ በተማሪዎች ላይ የሚያሳድረው ተጽእኖ ያሳድራል / እና ሁለተኛው ደግሞ በትህርት ቤት ውስጥ ያለው ህይወት የተማሪዎችን በራስ የመኩራት ላይ እንዴት ተጽእኖ ያሳድራል/ የሚሉትን ጥያቄዎችን በማንሳት ለመጀመሪያው ጥያቄ ያገኘው መልስ ከፍተኛ በራስ የመኩራት ያላቸው ተማሪዎች ዝቅተኛ በራስ መኩራት ካላቸው ተማሪዎች በተሸለ ሁኔታ

ስኬታማ እንደሆኑ ማርች(1990)ን ዋቢ በማድረግ ይገልጻል፡፡ ለሁለተኛው ጥያቄ ደግሞ ስለ ትምህርት ቤታቸው አዎንታዊ ሐሳብ ያላቸው ተማሪዎች የመምህሩ እንክብካቤና በራስ መኩራት ላይ ተጽእኖ እንሚያሳድር ውልፎል(2004፡73) ሐይስሚዝና ሐንሰን(1990) በመጠቀስ ገልጸዋል፡፡

## 2.1.2.4. በራስ ያለመተማመን

እንደ ሒልቶንና ሐይደር(1992፡7) የስኬታማ ጸሐፊዎች በራስ መተማመን ባህሪያቸው ነው፡፡ ምክንያቱም በራስ መተማመናቸው የመጻፍ ክሂላቸውን የሚያጎልብት ነው፡፡ መጻፍ በእጅጉ አስደሳችና አጥጋቢ ብቻ ሳይሆን በእጅጉ ስኬታማም ሊሆን ይገባል፡፡ ሐርመር(2005) በበኩሉ በራስ የመተማመን ጉዳይ አስመልክቶ ለጥሩ መጻፍ በእጅጉ አስፈላጊ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ ኔማን(1995፡5) ‹‹ መጻፍ ብዙ እውቀትን ብቻ ሳይሆን ይህንን እውቀት የምንለማመድበትን በራስ መተማመንንም ይፈልጋል፡፡›› በማለት ይገልጻሉ፡፡

በድጋሚ ኔማን(1995፡7) ለጽህፈት ችግሮች ሁለት መፍትሂዎችን ሠንዝሯል፡፡ በአጠቃላይ እነዚህን የጽህፈት ችግሮች በእደ ጥበብ ተኮር (Craft center) እና ተጽእኖ ተኮር (affect Center Solution) አማካኝነት ማስወገድ እንደሚቻል ኔማን (1995)ይገልጻሉ፡፡ እደ ጥበብ ተኮር የተማሪዎችን ጽህፈት ስህተት ማስተካከልና መተቸትን ሲያጠቃልል ጭንቀትን ከመጨመሩ አንጻር ውድቅ የሆነ ነው፡፡ ተጽእኖ ተኮር መፍትሂ ግን በአጠቃላይ የመማር ሂደቱ ላይ አጽንኦት የሰጠ ነው፡፡ ይህም ቀዳሚ ግቡ ተማሪዎችን ለጥሩ ጽሑፍ የሚያበቁ አስፈላጊ ክሂሎችን እንዲይዙ መርዳት ብቻ ሳይሆን የጽህፈት ማስተማሪያ ስልቶች የሚሰጧቸውን እድል በመጠቀም ስለራሳቸውና ስለአለም የተሻለ እንዲረዱ ማድረግ ነው፡፡

እንደሰሎሞን (1997፡84-265) በጽህፈት ውስጥ የሚታዩ ዘውትራዊ ችግሮች የሚባሉትን እንደሚከተለው ዘርዝሯል፡፡

## 2.1.2.5 የቃላት አጻጻፍ ችግር

በዝቅተኛ ክፍሎችም ሆነ ከፍ ባሉ የክፍል ደረጃዎች የሆሄያትን ቅርጽ በትክክል የማይጽፉ ተማሪዎች ቁጥር ቀላል አይደለም፡፡ ችግሩ ከትምህርት ቤት ውጭም በስራ አለም ላይ ይታያል፡፡ ከእነዚህም ውስጥ ‹‹ዲቃላ›› ሆሄያትን በሳብዕ ቅርጾች የመተካት ሲሆን፣ በኋላ -

በሆላ፣ ቋንቋ - ቆንቆ፣ አኗኗር - አኖኖር  የሚሉት በምሳሌነት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ ሌላኛው ችግር ደግሞ ‹‹አ››ን በ‹‹ሀ›› መተካት ነው፡፡ ለአብነትም አቅም - ሀቅም፣ አንድ - ሀንድ፣ አያሌ - ሀያሌ፣ የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ ሌላው በዚህ ደረጃ እንደችግር የሚጠቀሰው አንደኛ መደብ ነጠላ ቁጥር የሚያሳየውን የባለቤት አጸፋ ‹‹ሁ››ን በ‹‹ው›› መተካት ነው፡፡እመጣለሁ - እመጣለው፣ ሰጥቻታለሁ - ሰጥቻታለው፣ እሔዳለሁ - እሔዳለው  እና ሸኘሁህ - ሸኘውህ የሚሉት ቃላት በምሳሌነት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ በተጨማሪም አክብሮት አመልካቹን ‹‹ዎ››ን መዋጥ ሌላኛው ችግር ነው፡፡ ለምሳሌ መጣልዎ - መጣሎ፣ አለልዎ - አለሎ፣ ድርጅትዎ - ድርጅቶ እና ሰርግዎ - ሰርጎ፡፡ ሌላው ችግር አንደኛ መደብ ነጠላ ቁጥር አመልካችን የተሳቢ አጸፋ ‹‹ኝ››ን ያለቦታው መጠቀም ነው፡፡ ለምሳሌ ነገርኩት - ነገርኩትኝ፣ ወሰድኩት - ወሰድኩትኝ፡፡ በተጨማሪም ሁለት ሆሂያትን ነጣጥሎ መጻፍ ሲገባ አንዱን በአንዱ ውስጥ በማካተት ለየት ያለ ቅርጽ መፍጠር ሌላኛው ችግር ነው፡፡ የመጣችሁ - የመጣቹ፣ ልጆቻችሁ - ልጆቻቹ፣ ዕቃችሁ - ዕቃቹ፣ አይደላችሁም - አይደላቹም ወዘተ ለአብነት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ የመጨረሻው ሆሂያትን መግደፍ ነው፡፡

ለምሣሌ፡-  መጥቷል - መቷል፣ እሺህ - ሺህ(ክ)፣ አደረገ - አረገ፣ አንዳንድ - አንዳድ፣ ሰጥተን - ሰተን፣ እያወቅኩ - እያወኩ፡፡

ሁለተኛው የቃላት አጻጻፍ ችግር ነው፡፡ ከእነዚህም ውስጥ በግራና በቀኝ ህዳግ ላይ የአንድ ቃል አካል የሆነውን አንድ ሆሄ ለብቻው መጻፍ፡፡እንደሚከተለው ማለት ነው፡፡

| |
|---|
| ሀ. ከገበያ የገዛችውን ጆንያ ለ<br>ህቷ ሰጠቻት |
| ለ.ከገበያ የገዛችውን ጆንያ ለህ<br>ቷ ሰጠቻት |

ሌላው በዐ.ነገር ውስጥ ቃላትን ስንደረድር አንዱን ቃል ከተከታዩ ከቀዳሚው በመጠኑ ራቅ አድርጎ ያለመጻፍ ችግር፡፡ ማገዶውንሰብስባበገመድ አሰረችው እና አንድ ሽብር ስጠኝ የሚሉት ዐ.ነገሮች ለአብነት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

ሦስተኛው የቃላት መረጣ ችግር ነው፡፡ እነዚህም የአንባቢን ማንነት ያለመለየት ፣ የጽሁፍን አላማ ያለመገንዘብ፣ ሐሳቡ የሚቀርብበትን ሁኔታ ያለማወቅ፣ ቃላት ድረታ፡-

ይህን ጉዳይ ከሚከተሉት ሁለት ነጥቦች አንጻር ማየት ይቻላል፡፡ እነሱም አንድን ቃል ደጋግሞ መጻፍ እና ተመሳሳይ ፍቺ ያላቸውን ቃላት ማካተት፡፡ ሌሎች ቃላት መረጣ ረገድ የሚተዩት ችግሮች የቃላት አቻዊነትን ያለመጠበቅ እና ግልጽ ቃላት ያለመጠቀም ናቸው፡፡

### 2.1.2.6 በዐ.ነገር ግንባታ የሚታዩ ችግሮች

በመጻፍ ወቅት በዐ.ነገሮች ውስጥ የሚታዩ ልዩ ልዩ ችግሮች አሉ፡፡ ከእነዚህም የመጀመሪያው የቁጥር አለመስማማት ነው፡፡ የቁጥር አለመስማማት ከሚታይባቸው ተዋቃሪዎች መካከል ባለቤትና ግስ በዋወናነት ይጠቀሳሉ፡፡ ለምሣሌ [በሠርጉ እለት የተገኙት እድምተኞች ቁጥር ብዙ ነበሩ፡፡] የዚህ ዐ.ነገር ግስ የሚያመለክተው ብዙ ቁጥርን ነው፡፡ ይሁንና የሚነገረው ግን በነጠላ ቁጥር ስለቀረበው ቃል [ቁጥር] ነው፡፡ ይህም በመሆኑ የተናጋሪው ሐሳብና ስለሱ የሚገልጸው ግስ በቁጥር አልተጣጣሙም፡፡ አንዱ ነጠላ፣ ሌላው ብዙ ናቸው፡፡

በሁለተኛነት የጾታ አለመስማማት ነው፡፡ ጾታ ለተሰኘው ሰዋስዋዊ ባህርይ ቅርጻቸውን የሚለዋውጡት ቃላት ስሞችና ቅጽሎች ናቸው፡፡ ስምምነቱ የማይታየውም እርስ በእርስ በሚናበቡ ተዋቃሪዎች ላይ ነው፡፡ ለምሣሌ [የኮረዳዋ ዉበት እዚህ ቀረሽ የማትባል ነች፡፡] በዚህ ዐ.ነገር ውስጥ የጾታ አለመስማማት ይታያል፡፡ ዐ.ነገሩ የሚናገረው ስለኮረዳ ሳይሆን ስለኮረዳ ውበት ነው፡፡ ‹‹ውበት›› የሚለው ቃል ደግሞ በዚህ አቋሙ ተባእታይ ነው፡፡ ስለዚህ የዐ.ነገር መቋጫ [ኮረዳዋ እዚህ ቀረሽ የማትባል ነች] ተብሎ መስተካከል ይኖርበታል፡፡ እንደዚህ የመሳሰሉ የጾታ አለመጣጣም ያለባቸውን ዐ.ነገሮች ማየት የተለመደ ነው፡፡ ችግሩ የሚከሰተው ዐ.ነገሩ የሚገልጸው ስለምንድነው የሚለውን ጥያቄ በቅድሚያ በውል ካለማጤን ነው፡፡ በአማረኛ ዐ.ነገሮች ከጾታ አለመስማማት ይልቅ የቁጥር አለመስማማት አየል ብሎ ይታያል በማለት ሰለሞን (1996፡147) ይገልጻል፡፡ ይሁንና በአንድ ዐ.ነገር ውስጥ ቁጥራዊም ሆነ ጾታዊ ችግር በአንድነት ሊከሰቱ እንደሚችሉ ያስገነዝባል፡፡

በሦስተኛነት የቅጥያዎች አገባብ ችግር ነው፡፡ የቅጥያዎች አገባብ የ‹‹ን››፣ የ‹‹የ›› እና የመስተዋድዶች አገባብ ችግርን ያጠቃልላል፡፡ የ‹‹ን›› አገባብ ችግር የሚከሰተው ትክክለኛው መገኛ ቦታው ሲጣረስ ነው፡፡ ይህም የመጀመሪያው በአንድ ዐ.ነገር ውስጥ

መስተአምር ያስከተለ ቀጥተኛ ተሳቢ ካለ ተሳቢ አመልካቹን ቅጥያ‹‹ን››ን ይወስዳል፡፡ ለምሣሌ ተማሪው[ልጅ-ኦች-ኡ-ን] ጠራቸው፡፡ በቅንፍ የተመለከትነው ቀጥተኛ ተሳቢ ነው፡፡ ይህ ተሳቢ መስተአምር [-ኡ] ስላስከተለ የተሳቢ አመልካቹን ቅጥያ [-ን]ን ወስዷል፡፡ ሁለተኛው መገኛ ቦታ በአንድ ዐ.ነገር ውስጥ አገናዛቢ አጸፋ ያስከተለ ቀጥተኛ ተሳቢ ካለ የተሳቢ አመልካቹን ቅጥያ ‹‹ን››ን ይወስዳል፡፡ ለምሣሌ መሐንዲሱ [ቤት-ኤ-ን] አየልኝ፡፡ በቅንፍ የተመለከትነው ቀጥተኛ ተሳቢ ነው፡፡ ይህ ተሳቢ አገናዛቢ አጸፋ [-ኤ]ን ስላስከተለ የተሳቢ አመልካቹን [-ን]ን ወስዷል፡፡ ይሁንና ይህ አገባብ ሲጣረስ ይታያል፡፡ ፈረሱ ጥሬኅ ይወዳል እና ሰው(ን) መጉዳት አያስፈልግም የሚሉት ለአብነት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

በዐ.ነገር ውስጥ የ‹‹የ›› አገባብ ችግር የሚከሰተው ደግሞ ጥገኛ ምዕላዱን ያለቦታው በማስገባታችን የሚፈጠር ስህተት ነው፡፡ ምክንያቱም የ[የ-] መጨመር ሐሳብን ግልጽ ለማድረግ ያግዛል፡፡ለምሣሌ፡- [የ]እኔ ቦታ፣ [የ]ጓደኛዬ መጽሐፍ እና [የ]እህቴ በግ ለአብነት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

ሌላው በዐ.ነገር አወቃቀር የሚታየው ችግር የመስተዋድዶች አገባብ ነው፡፡ ችግሩም የሚከሰተው መስተዋድዶችን ያለቦታቸው ማስገባትና በተገቢው ቦታቸው ላይ አለማስቀመጥ ነው፡፡ ለምሣሌ፡- በመንደራቸው አቅራቢያ [ወደሚገኝ ወደገበያ ቦታ] ሲያዘግም ነበር፡፡ በዚህ ዐ.ነገር ውስጥ በሚገኘው በቅንፍ የተመለከተ መዋቅር ውስጥ የመስተዋድዱ [ወደ-] አገባብ ትክክለኛ አይደለም፡፡ [ገበያ] የሚለው ስም ያለመስተዋድዱ መነገር አለበት፡፡ ይህም ማለት አጎላማሽ ስላለው መስተዋድዱ ወደአጎላማሽ ተንቀሳቅሷል፡፡ ስለዚህ ገበያ አቅጣጫ አመላካቹን [ወደ-]ሳይሆን [የ-]ን መውሰድ ነበረበት፡፡ ይህም ሲስተካከል [በመንደራቸው አቅራቢያ ወደሚገኝ የገበያ ቦታ ሲያዘግም ነበር] ይሆናል፡፡

በተጨማሪም በዐ.ነገር ውስጥ ከሚታዩ ችግሮች አንዱ የጥገኛ አረፍተ ነገሮች አቀማመጥ ነው፡፡ ይህ ችግር የሚከሰተው ጥገኛ ዐ.ነገሮቹን በተገቢ ቦታቸው ላይ ካለማስቀመጥ ነው፡፡ ‹‹ነጋዴው ወደጎንደር ነው የሚሄደው፡፡›› እና ‹‹ዘፋኙ አምና ነበር የተሸለመው፡፡›› የሚሉት ለአብነት ይጠቀሳሉ፡፡ እነዚህ ዐ.ነገሮች ሲቃኑም ‹‹ነጋዴው የሚሄደው ወደጎንደር ነው፡፡›› እና ‹‹ዘፋኙ የተሸለመው አምና ነበር፡፡›› የሚሉትን ይሆናሉ፡፡

ሌላው የተዋቃሪዎች እንቅስቃሴ ችግር በዐ. ነገር ውስጥ ሊከሰት ይችላል፡፡ እንቅስቃሴውም በራሱ በዐ.ነገር ውስጥ ወይም ከዐ.ነገሩ ውጪ ሊካሄድ ይችላል፡፡ለምሣሌ ‹‹ታተሪው ገበሬ

[በሬዎቹን] ለአንድ ሐብታም ነጋዴ [……..] ሸጣቸው፡፡›› የሚለው በዐ.ነገር ውስጥ የተካሄደ የተዋቃሪ እንቅስቃሴ ነው፡፡ ‹‹[በጠመንጃ] አዳኞቹ [……] ዝሆኑን ገደሉት፡፡›› የሚለው ዐ.ነገር ደግሞ ከዐ.ነገር ውጭ የተደረገን የተዋቃሪዎችን እንቅስቃሴን ያመለክታል፡፡ ይህም በመሆኑ ዐ.ነገሮቹ በያዙት ሐሳብ ላ አሻሚነት ታይቶባቸዋል፡፡

በመጨረሻም በዐ.ነገር ውስጥ ከሚታዩ ችግሮች የሐሳብ አፍራሽ ጥገኛ ምዕላድን በተገቢው መንገድ ያለመጠቀም ነው፡፡ ይህም የሚከሰተው ዋንኛ ሃሳብ አፍራሽ ጥገኛ ምዕላድ አል-ን በተገቢው ቦታ ካለመጠቀም ነው፡፡ ይህም የሐሳብ አፍራሽ ምእላዱን በአንድ ዐ.ነገር ውስጥ ሁለት ቦታ ላይ በሚገባበት ጊዜ ሐሳብን ሊያዛባ መቻሉ ነው፡፡ ለምሣሌ፡- ‹‹ሃላፊው ጉቦ አልተቀበልኩም አላለሉም፡፡›› የሚለውን ዐ.ነገር ብንወስድ ‹‹ተቀብያለሁ›› ብለዋል እንደማለት ሊሆን ይችላል፡፡ ከዚህ የምንረዳው በአንድ ዐ.ነገር ውስጥ ሁለት እልት ግሶች ካሉ ሐሳቡ አሉታ መሆኑ ቀርቶ አዎንታ እንደሚሆን ነው፡፡

ሌላው በዐ.ነገር ውስጥ የሚታየው ችግር የአያያገሮች አገባብ ነው፡፡ ይህም ተገቢ አያያገሮችን ያለመጠቀም ችግር ነው፡፡ የችግሩ ሰበብ ተያያዥ ሐሳቦችን በወጉ አጢኖ የሚስማማቸውን ያለመምረጥ ይመስላል፡፡ ለምሣሌ፡- ተማሪው ከትምህርት ቤት ተባሯል፤ [በዚህ የተነሳ] ወላጆቹ ወደትምህርት ቤቱ አስተዳደር ቀረቡ፡፡ በቅንፍ የተመለከትነው አያያዥ ያለቦታው የገባ ነው፡፡ ይህ አያያዥ የሚያስፈልገው የምክንያትና የውጤት ትስስር በሚታይባቸው ሐሳቦች መካከል ወይም /እንዲህ በመሆኑ እንዲህ ሆነ/ ብለን ስንናገር ነው፡፡

በተጨማሪም ሥርአተ ነጥቦችን በአገባቡ ያለመጠቀም ችግር በዐ.ነገር ውስጥ ሊታይ ይችላል፡፡ ይህም በዐ.ነገር ግንባታ ወቅት ስርአተ ነጥቦችን በአገባቡ አለመጠቀምና ጭራሹንም ያለመጠቀም ችግር ሊከሰት ይችላል፡፡ ለምሣሌ፡- አንድ ሽ ብር [አንድ ሽብር] የሚለውን ብንመለከት በቃላት መካከል ሁለት ነጥብ ካላስቀመጥን ወይም ቃላቱን አራርቀን ካልጻፍን በመልእክቱ ትልልፍ ላይ መሰናክል ሊያጋጥም ይችላል፡፡ በሌሎችም ስርአተ ነጥብ አጠቃቀም ላይ በዐ.ነገር ግንባታ ሒደት ችግር ሊፈጠር ይችላል፡፡

### 2.1.2.3 በአንቀጽ ግንባታ ወቅት የሚታዩ ችግሮች

በአንቀጽ ግንባታ ወቅት ሊጤኑ የሚገቧቸው መሠረታዊ ጉዳዩች አንዱ የአረፍተ ነገሮች ርዝማኔ ነው፡፡ ይሁንና ለዚህ ጽሁፍ አጫጭር፣ ለዚህ ደግሞ ረጃጅም ዐ.ነገሮች ይስማሙታል ብሎ መደምደም ይቸግራል፡፡ ይሁንና አጫጭርም ሆነ ረዣዥም ዐ.ነገሮችን አብዝቶ መጠቀም አይመከርም፡፡ ምክንያቱም አጫጭር ዐ.ነገሮችን ብቻ በአንቀጽ ውስጥ ማካተት የሐሳብ መቆራረጥን ሊያስከትል ይችላል፡፡ የአንቀጽ አካልነታቸው እንዲታይ ሐሳቡን ለማያያዝ መሞከር ያስፈልጋል፡፡ አጫጫር ዐ.ነገሮች ለጀማሪዎች ማለማመጃነት እንደሚጠቅሙ የድርሰት መምህራን ይገልጻሉ፡፡ በተቃራኒው አንቀጽን በረዣዥም ዐ.ነገሮች መገንባት የራሱ ችግር አለው፡፡ ይህም ለሰዋስዋዊ ስህተት እንደሚያጋልጥና የሐሳብ መምታታት ሊፈጥር ይችላል፡፡

ሌላው በአንቀጽ ግንባታ ወቅት የሚታየው ችግር የሐሳብ ስፋት ነው፡፡ አንቀጽ ከድርሰት ጋር ሲነጻጸር ወርደ ጠባብ ነው፡፡ የሚይዘውም አንድ ዋና ሐሳብ ብቻ እንደሆነ ይታወቃል፡፡ ይህም በመሆኑ የአንድ አንቀጽ ሐሳብ ቶሎ የሚጠናቀቅ እንጅ በአጭሩ የማይገታና በርካታ ጉዳዩችን ጋባዥ መሆን የለበትም፡፡ ስለዚህ አንድን አንቀጽ ስንወጥን የሐሳቡን ስፋትና ጥበትም አስቀድመን ማጤን ይኖርብናል፡፡

በመቀጠልም አጠራጣሪ ሀሳብን የያዙ ዐ.ነገሮችን መጻፍ በአንቀጽ ግንባታ ወቅት ሊታዩ የሚችሉ ችግሮች ናቸው፡፡ እንደዚህ አይነት ዐ.ነገሮች የአንባቢን ስሜት ተቆጣጥረው የመያዝ አቅም አይኖራቸውም፡፡ አንቀጹንም ፍዝ ያደርጉታል፡፡

በተጨማሪም በአንቀጽ ግንባታ ወቅት የሚታየው ችግር የዐ.ነገሮች ብዛት ነው፡፡ በአንድ አንቀጽ ውስጥ ሊገኙ የሚገባቸውን ዐ.ነገሮች መጠን የሚወስነው የሚተላለፈው ሐሳብ ስፋትና ጥበት ሊሆን እንደሚችል ይታመናል፡፡ አንቀጽ ቁጥብ በመሆኑ ግን በተወሰኑ ዐ.ነገሮች ሊገነባ ይገባል፡፡ ስለሆነም ልናስተላልፍ የምንፈልገውን ሐሳብ ከአምስት እስከ አስር በሚደርሱ ዐ.ነገሮች ብንገልጽ መልካም መሆኑን ሰለሞን (1996፡210) በዚህ ዙሪያ የተጻፉ ጥናቶችን ዋቢ በማድረግ ይገልጻል፡፡

ሌላው በአንቀጽ ግንባታ ወቅት ሊታይ የሚችለው ችግር የምክንያትና የውጤት ትስስርን አለመጠበቅ ነው፡፡ ይህም በአንድ አንቀጽ ውስጥ ከሚገኙት ዐ.ነገሮች የተወሰኑት የምክንያትና የውጤት ትስስር ሊታይባቸው ይችላል፡፡ በሰበብነትም ሆነ በውጤትነት

ያቀረብናቸው ሐሳቦች ሊታመኑ ይገባል፡፡ ይህ ካልሆነ ሰበቡና ውጤቱ የጠበቀ ዝምድናን ላያሳዩ ይችላሉ፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ በአንቀጹ ግልጽነት ላይ ችግር ሊፈጠር ይችላል፡፡

በተጨማሪም ሐሳብን ያለማቋረጥ ችግር በአንቀጽ ግንባታ ላይ ችግር ሊፈጥር ይችላል፡፡ በዚህ ምክንያት ዐ.ነገሮችን ግልጽና ቀጥተኛ መልእክት እንዳያስተላልፉ ሊያደርግ ይችላል፡፡ ይህ ከሆነ የተጀመረው ሐሳብ ሳይጠናቀቅ ሌላ አዲስ ሀሳብ የሚጨመርበት ከሆነ ማደናገሩ አይቀሬ ነው፡፡

በመቀጠልም ሐሳብን በወጉ ያለማብራራት በአንቀጽ ግንባታ ወቅት ችግርን ሊፈጥር የሚችል ጉዳይ ነው፡፡ ይህም የሚፈጠረው በአንቀጽ ውስጥ የሚገኘው ዋናው ሐሳብ በወጉ ሳይብራራ ሲቀር ነው፡፡ ለዚህም ችግር ዋና ሐሳብን የሚያጎለብቱ ዝርዝር ነጥቦችን ከተለያዩ አቅጣጫዎች አንጻር ማቅረብ ያስፈልጋል፡፡

የመጨረሻው በአንቀጽ ግንባታ ወቅት ችግር ሊፈጥር የሚችለው ጉዳይ ሐሳብን በጅምር መተው ነው፡፡ ይህም በመሆኑ የአንቀጹ ይዘት ያልተሟላ፣ ቅርጹም ያልተስተካከለ ይሆናል፡፡

#### 2.1.2.4 በድርሰት ግንባታ ወቅት የሚታዩ ችግሮች

በድርሰት ግንባታ ወቅት ሊጤኑ ከሚገባቸው መሠረታዊ ጉዳዩች አንዱ የምንጽፍበትን ጉዳይ አስቀድመን ያለመወሰን ችግር ነው፡፡ ይህ ከሆነ ጽሁፉችን ከሚያጠነጥነው አቢይ ጉዳይ ልንወጣ እንችላለን፡፡ ሁለተኛው ችግር ለምን እንደምንጽፍ ያለማወቅ ነው፡፡ ይህ ከሆነ ከጽሁፉ አላማ ልንወጣ እንችላለን፡፡ ሦስተኛው ችግር ለማን እንደምንጽፍ ያለማወቅ ነው፡፡ ይህ ካሆነ ለአንባቢው የሚመጥነውን ጽሁፍ ማዘጋጀት ያዳግታል፡፡ አራተኛው ጉዳይ የድርሰቱን(የጽሁፍን) አይነት በቅድሚያ መወሰን ያለመቻል ነው፡፡ አምስተኛው አዕምሮን በበቂ ንባብ ያለመሙላት ችግር ነው፡፡ ይህ ከሆነ ጥሩ ጸሀፊ ልንሆን አንችልም፡፡ ስድስተኛው ስለምናውቀው ነገር ያለመጻፍ ችግር ነው፡፡ በመሆኑም የመረጃ እጥረት ሊያጋጥም ይችላል፡፡ ሰባተኛው የምንጽፍበትን ቋንቋ ሰዋስዋዊ ህግ ያለመገንዘብ ችግር ነው፡፡ በመሆኑም በሰዋስው ስህተት ምክንያት መልእክቱ ሊደናቀፍ ይችላል፡፡ ስምንተኛው የሐሳቦችን ቅደምተከተል ያለመወሰን ችግር ነው፡፡ ስምንተኛው ጉዳይ የድርሰቱን መነሻና መድረሻ በአግባቡ ያለማደራጀት ችግር ነው፡፡ ይህ ከሆነ የድርሰቱ ሐሳብ በየአቅጣጫው ተበትኖ እንዲቀር ሊያደርግ ይችላል፡፡ ዘጠነኛው ጉዳይ የሚነሱ

ነጥቦችን ምንነትና አደረጃጀት ያለማሰላሰል ነው፡፡ ይህ ካሆነ የጽሁፉን ሥራ ለመወጠንና ለማጠናቀቅ አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል፡፡ የመጨረሻው በድርሰት ግንባታ ሒደት ችግር ሊፈጥር የሚችለው የአርትኦት ሥራን ያለማከናወን ነው፡፡ ይህ ከሆነ ጽሁፉ ላይ የጥራት ችግር ሊገጥም ይችላል፡፡

በአጠቃላይ እነዚህ ለአብነት ያህል ይቅረቡ እንጅ ችግሩ ከዚህም የበረታ መሆኑን ሰለሞን( 1997፡86) ይገልጻል፡፡

በመሆኑም ከላይ እንደቀረቡት ጥናቶችና ጽሁፎች መሠረት የተጠቀሱት የጽህፈት ግድፈቶችና ስህተቶች  ከታላላቅ ጸሐፊዎች እስከ ጀማሪ ተማሪዎች ድረስ ሊከሰቱ የሚችሉና የጽሑፍን አጠቃላይ ገጽታ ሊያበላሹ የሚችሉ እንደሆኑ መረዳት ይቻላል፡፡ አጥኝውም በማስተማር ሙያው ውስጥ በተደጋጋሚ ጎልተው ተማሪዎች ላይ ከሚታዩ የጽህፈት ግድፈቶች ውስጥ በዋንኛነት እነዚህ እንደሆኑ ማስተዋል ችሏል፡፡ በመሆኑም እነዚህ የጽህፈት ችግሮች ተገቢውንና ስልታዊ መፍትሄን እንደሚፈልጉ አጥኝው መገንዘብ ችሏል፡፡

### 2.1.3 የመጻፍ ትምህርት ማስተማሪያ ዘዴዎች ሚና

ክሪስቲሶን(1990፡146) በሁለተኛ ቋንቋ የመጻፍ ትምህርት ማሰተማር ዘዴዎች ያላቸውን ሚና በተመለከተ ሁለት ጥያቄዎችን ጠየቀ፡፡ የመጀመሪያው ጥያቄ ከመጻፍ ማስተማሪያ ዘዴዎች  ለውጥ ምን ጥሩ ውጤት ይጠበቃል? ሲሆን፤ ሁለተኛው ጥያቄ ደግሞ ለምድነው ወደ ለውጥ የምንገባው? የሚሉት ናቸው፡፡

እነዚህ ሁለት ጥያቄዎች የመጻፍ ማስተማሪያ ዘዴዎችን ከመጠቀማችን በፊት በማንኛውም መምህር የሚቀርብ ጥያቄ ነው፡፡ ይሁንና አብዛኞቹ ምርምሮች የመጻፍ ማስተማሪያ ዘዴዎች በተማሪዎች የመጻፍ አቅም ላይ ያላቸው ተጽእኖ አስመልክቶ አዎንታዊም አሉታዊ ውጤት እንዳላቸው ያመለክታሉ፡፡

እንደ ሒስማኖጉሉ(2005) ጥናት የቁጥጥር፣ መርና የነጻ መጻፍ ማስተማሪያ ዘዴዎች ለሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች የመጻፍ አቅማቸውን በማጎልበት ረገድ አዎንታዊ ውጤት እንዳላቸው ይገልጻል፡፡ እስማኤል(2008)ና በሊንዳ(2006) በጥናታቸው ሒደታዊ መጻፍ

ማስተማሪያ ዘዴ የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ በማጎልበት ረገድ አዎንታዊ አንድምታ እንዳለው ይገልጻሉ፡፡

ይሁንና አንድ ስኬታማ የመጻፍ ማስተማሪያ ዘዴ የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታን ለማጎልበት ያላቸውን ሚና ለመለካት ስነልሳናዊ፣ ማህበራዊና ስነልቦናዊ ርስቶችን (Domains) ሊያሻሽሉ እንደሚገባ በሁለተኛ ቋንቋ መጻፍ ማስተማር ዘዴ ላይ የተሰሩ ጥናቶች ያመለክታሉ፡፡

#### 2.1.3.1 ማህበራዊ ርስቶችን ማሳደግ

የመጻፍ ማስተማሪያ ዘዴዎችን መጠቀም የመምህሩ የማስተማሪያ ስልት ቀዳሚ ጉዳይ ነው፡፡ ከዚህ አቅጣጫ ዊሊያምስ (2003፡139) እንደሚያመለክተው ‹‹በተግባራዊ ማህበረሰብ ውስጥ ወጣቶችን ለስኬታማ ህይወት ለማዘጋጀት ሥራዬ ነው ብሎ የሚያምን መምህር የመጻፍ ማስተማሪያ ዘዴዎችን ማህበራዊና ትምህርታዊ ጠቀሜታዎች መገንዘብ ይጠበቅበታል›› በማለት ይገልጻል፡፡

#### ሀ.መስተጋብርን ማጎልበት

እንደ ገንቢያውያን እይታ መሰረት የተማሪዎች ፈጣን ፍችን የመገንባት ጉዳይ ነው፡፡ ፖፕና ኪን(1981)፣ ሱዝርላንድ(1992)፣ ቶምስና ሐሪ(1985)፣ ዊሊያምና በሪንዳን(1999) እንደጠቀሱት ማህበራዊ ገንቢያዊያን ቋንቋን የመማር አቀራረብ ማህበራዊ ሒደት ነው፡፡ ከዚህ አውድ አንጻር ፍችዎች ሊገነቡ የሚችሉት ከሌሎች ግለሰቦች በምናደርገው መስተጋብር አንጻር ነው፡፡ በመሆኑም ቀዳሚ ጠቀሜታ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ ዊሊያምስና በሪንዳን(1999) እንደገለጹት የፍችዎች መስተጋብርና ስምምነት ለስኬታማ ቋንቋ መማር ከፍተኛ ጠቀሜታ ናቸው፡፡ በተልመዷዊ የመማር ማስተማር ሒደት የፍችዎችን ስምምነትና ግንኙነት በተማሪዎች መካከል እንዲኖር ያላደረጉና በጥቂቱ ብቻ ያካተቱ ናቸው በማለት ፒካ(1987) ፒካና ዳውቲይ(1992)ን ጠቅሶ ገልጸዋል፡፡

እንደ ሊትል ውድ(2003) ‹‹የመምህሩ ሚና ነው የክፍል ውስጥ መስተጋብርን የሚወስነው›› በማለት ትገልጻለች፡፡ በተለምዷዊ ማስተማሪያ ዘዴ የሚመሩ ክፍሎች በተቃራኒው መምህሩ ዋና ተዋናይ ሲሆን፣ ተማሪን ያማከለው ዘዴ ግን ተማሪዎች እርስ በራስ መስተጋብር የሚፈጥሩበትን እድል ይሰጣል፡፡ ሐሳባቸውን እንዲለዋወጡ፣ እንዲወያዩ

እድል ይሰጣቸዋል፡፡ ይህ ደግሞ በተለይም ጭንቀትን ይቀንሳል፡፡ በመሆኑም የመጻፍ ማስተማሪያ ዘዴዎች ይህንን እድል የሚፈጥሩ መሆን ይጠበቅባቸዋል፡፡

ውልፎልክ(2004፡41) ተማሪዎች ከመምህራቸው ወይም ከጓደኞቻቸው ጋር ያላቸው መስተጋብር ጠቀሜታው‹‹አስተሳሰባቸውን በራሳቸው ለመመዘንና ምጋቤ ምላሽ ለመቀበል ዝግጁ ለመሆን፣ በተግባር የሚፈቱ ችግሮችን የመስራት አቅማቸውን ለመለየት›› ጠቃሚ እንደሆነ አጽንኦት ሰጥቶ ይገልጻሉ፡፡ እንደ ውልፎልክ(2004፡42) ‹‹ከሌሎች ጋር ተግባቦትን ማድረግ የአስተሳሰብ አቅማቸውን ለመጠቀም ፣ ለመመዘንና አንዳንዴም ለመለወጥ ያስችላቸዋል፡፡›› በማለት ያስገነዝባሉ፡፡

## ለ. ተሳትፎን ማጎልበት

እንደ አርኖልድ(1999፡2) ‹‹ ተማሪዎች አንድን ተግባር ለማጠናቀቅ ወይም ወደ ምርት ለማሳደግ ከእያንዳንዱ አባላት አስተዋጽኦ ውጭ ሊሳካ አይችልም›› በማለት ይገልጻል፡፡ይህም የሚመክረን ተማሪዎች በአንድ በኩል ነጻ መሆን ሲኖርባቸው በሌላ በኩል ደግሞ እርስ በራሳቸው ጥገኛ ናቸው፡፡ በአጠቃላይ የክፍሉ ተማሪዎች ስኬት የእያንዳንዱ ተማሪ ስኬት ድምር ውጤት ነው፡፡ በመሆኑም የመጻፍ ማስተማሪያ ዘዴዎች የተማሪዎችን ተሳትፎ በማፋጠን ለስኬታማ የቋንቋ ትምህርት ግብ ሊሆኑ ይገባል፡፡

## ሐ. ማህበራዊ ክህሎትን ማጎልበት

ስኬታማ የመጻፍ ማስተማሪያ ዘዴዎች የተማሪዎችን ‹‹የማጣራት፣ የተጣራውን የመልቀም፣ መረዳታቸውን ለማረጋገጥ፣ ብዙ መረጃዎችን አሳማኝ የማድረግና የመስማማት ክህሎታቸውን ሊያጎለብቱ ይገባል፡፡ እንዲሁም ተማሪዎችን በመጠየቅ፣ በማዳመጥ፣ ወይም ትኩረት በመስጠት፣ ፈጣን ተሳታፊ በመሆን ወዘተ የመሳሰሉትን መስተጋብራዊ ክህሎታቸውን ሊያዳብሩ ይገባል፡፡›› በማለት አርኖልድ(1999፡3) ይገልጻል፡፡

## 2.1.3.2 ስነልቦናዊ ጠቀሜታ

ብራዎን(2000፡145) ‹‹አዕምሯዊም ሆነ ስሜታዊ ክንውኖች በራስ ከመኩራት፣ በራስ ከመተማመን፣ ለክንውኑ ካለን አቅምና እውቀት ጫናዎች ውጭ ስኬታማ ሊሆኑ አይችሉም›› በማለት ይገልጻል፡፡ ይህም የሚያስረዳ እነዚህ ነገሮች ለስኬታማ መማር ያላቸውን ጉልህ ሚና ነው፡፡

በመሆኑም በመጻፍ ማስተማሪያ ዘዴዎች ላይ የተሰሩ ምርምሮች እንደሚያመለክቱት ስኬታማ የመጻፍ ማስተማሪያ ዘዴዎች የተማሪዎችን በራስ መኩራትን፣ በራስ መተማመንን የሚያሳድጉና ጭንቀትን የሚቀንሱና ጠንካራ የቋንቋ መማር ተነሳሽነትን የሚፈጥሩ መሆን ይጠበቅባቸዋል፡፡›› በማለት ኦክስፎርድ(1990) ይገልጻሉ፡፡

### 1.ጭንቀትን መቀነስ

እንደ ክራዳል(1999) ‹‹ውድቀትን መፍራት ለተማሪዎች ስኬት በእጅጉ አደገኛና አስጊ ከሚባሉት አንዱ ነው፡፡ ይህንን አደገኛ ነገር ለመቋቋም ደግሞ ሐሳብን የማውጣጣት፣ ከመምህራንና ከተማሪዎች ጋር መስተጋብር መፍጠር፣ ክንውናቸውን ለሙሉ ክፍሉ ከማቅረባቸው በፊት ትችትን እርስ በእርስ የመተራረም እድሎችን መፍጠር ያስፈልጋል፡፡ የትኛውም ስኬታማ የማስተማሪያ ዘዴ ለእንደዚህ አይነት ጥሩ አየር በመፍጠር ጭንቀትን ሊቀንስ ይገባል፡፡ እንደ ክራዳል(1999)‹‹የማሰብ ጊዜ፣ ደጋግሞ የማስታወስና ምጋቤ ምላሽ የመቀበል መፍጠር በስኬታማነት ጭንቀትን በመቀነስና ቋንቋን የመማር ፍላጎትን የመጨነር ውጤትን ሊያመጡ ይገባል፡፡›› በማለት ይገልጻሉ፡፡

ኦክስፎርድ(1990፡142) በቋንቋ መማር ውስጥ ጭንቀት ያለውን አቅም ትኩረት መስጠት እንደሚገባ ሲያስቀምጡ ‹‹ጭንቀታም ተማሪዎች በራሳቸው ወይም በሌሎች ሰዎች ሂስ በቀላሉ ሊወድቁ ይችላሉ፡፡ በመሆኑም ይህን ጭንቀት በመቀነስ ረገድ የማስተማሪያ ዘዴዎች ቀላል የማይባል ሚናን ይጫወታሉ፡፡›› በማለት ይገልጻሉ፡፡

### 2.መነሳሳትን መጨመር

ብዙ መምህራን የመነሳሳት ትርጉም ውስብስብ እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡ ለምሳሌ ሲዘርስና ዶርኒይ(2005)፣ ፊልድማን(1997)፣ ማስጎሬትና ጋርድነር(2003)ና ስፖልስኪይ(2000) ተጠቃሽ ናቸው፡፡ በመሆኑም መነሳሳት ‹‹የሜታ አዕምሯዊ(meta Conginative) አላባ በመሆኑ ራስን በመቆጣጠር የመማር ሒደት(Self regulatory) ከፍተኛ ሚናን የሚጫወት ነው፡፡›› በማለት ኦምሌይና ቻሞት(1990፡160) ጆንስ(1987)ን በመጥቀስ ይገልጻሉ፡፡በታላሚው ቋንቋ የተማሪዎችን ብቃት በማጎልበት ከፍተኛ ተጽእኖ እንደሚያሳድር ውልፎልክ(2004፡42) ጋርድነር(1989)ንና ሌሎችን ጠቅሶ ገልጸዋል፡፡ ስለሆነም ‹‹የመማር ተነሳሽነት የተማሪዎችን ክህሎት ለማጎልበት አስፈላጊና ቀዳሚ ነገር ነው፡፡›› በማለት ኦሜልይና ቻሞት(19፡184) ፓሪስ(1988)ን ጠቅሰው ይገልጻሉ፡፡

ማዬርስ(1999፡65) ኩንዳ(1990)ን በመጥቀስ ‹‹ሙከራዎች እንደሚያረጋግጡት የመነሳሳት ሞተር የአዕምሮ ማሽናችን ሐይል ነው›› በማለት አስቀምጧል፡፡

በቋንቋ መማር መነሳሳት ያለው ሐይል የላቀ ነው፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ በተማሪው የመማር ምርጫ ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ እንደ ኦክስፎርድ(1990፡13)እንደሚያመለክቱት ከፍተኛ መነሳሳት ባላቸው ተማሪዎች ጥቅም ላይ ሚውሉ ዘዴዎች ጥቂት ነሳሽነት ባላቸው ተማሪዎችን ለማስተማር ከዋሉት ዘዴዎች ይልቅ በከፍተኛ ጠቃሚ ሆነዋል፡፡›› በማለት ይገልጻሉ፡፡ ይህንኑ ሐሳብ ሲያጠናክሩም ‹‹ለግለሰባዊ ተግባራት አዲስ ቋንቋን የሚማሩ ተማሪዎች ለድግሪ ማሟያነት ከሚማሩ ተማሪዎች በላይ የተለያዩ ዘዴዎችን ይጠቀማሉ፡፡›› በማለት ያስረዳሉ፡፡ እነደ ሼሐን(1989) የመማ ር ማስተማር ሁኔታዎች የተማሪዎች መነሳሳት ላይ በእጅጉ ተጽእኖ ያሳድራሉ፡፡ በመሆኑም የመጻፍ ማስተማሪያ ዘዴዎች የተማሪዎችን መነሳሳት በመጨመር ረገድ ሚና ማረጋገጡ አንዱና ዋነኛ ጉዳይ ነው፡፡

### 3. በራስ መኩራትን መጨመር

ለከፍተኛ የትምህርት ውጤት አዎንታዊ ተጽእኖ ከሚያሳድሩት አንዱ በራስ መኩራት ነው፡፡ የራሱን ሚና እንደተጫወተና አብዛኞቹ የስነልቦና ባለሞያዎችም ይህንን ሚናውን አመስግነዋል፡፡ እውነታውም በራስ መኮራትና በትምህርት ውጤት መካከል አዎንታዊ ተዛምዶ እንዳለ ይጠቁማሉ፡፡ እንደ ማዬርስ(1999፡22) ‹‹በከፍተኛ በራሳቸው የሚኮሩ ተማሪዎች በራሳቸው ከማይኮሩ ተማሪዎች በተሸለ ሁኔታ ከፍተኛ ውጤትን አስመዝግበዋል፡፡ የተማሪው የክፍል ውስጥ አስተዋጽኦ መጠን ተማሪው ስለራሱ ጥሩ ምስል እንዲኖረው ይመራል፡፡›› በማለት ይገልጻሉ፡፡

የትምህርት ውጤት አንድም በራስ መኩራት ውጤት ሲሆን፤ መንስኤም ነው ለማለት ማየርስ(1999፡22) ‹‹ከፍተኛ የትምህርት ውጤት ስለራስ ምስል ሁኔታዎችን ይፈጥራል፡፡›› በማለት ይገልጻሉ፡፡ ይሁንና ማይርስ(1999፡22) እነ አጎስተነሊና ሌሎች(1992)፣ ብራዎንስንና ጋላገር(1992)ን በመጥቀስ አዎንታዊ ጎን እንዳለው ሁሉ አሉታዊ ጎንም እንዳለው ያስረዳል፡፡ አዎንታዊ ጎኑም እራስን በማጋነንን ከሌሎች የበላይነት ስሜት እንዲሰማን በማድረግ ሌሎችን ከራሳችን በታች እንድንቆጥር ያደርጋል፡፡ ይህ ብቻ ሳይሆን በተማሪዎች ዘንድ ተቀባይነትን ማጣት በራሱ በራስ መኩራትን ይቀንሳል በማለት ያስረዳሉ፡፡

በመሆኑም የመጻፍ ማስተማሪያ ዘዴዎች የተማሪዎችን በራስ መኩራትን በማሳደግ ተማሪዎችን ለጥሩ መጻፍ ሊያበቋቸው እንደሚገባ ማየርስ 1999፡42) ይጠቅሳሉ፡፡ በተመሳሰይም ዉልፎልክ(2004) የመጻፍ ማስተማሪያ ዘዴዎች በተማሪዎች በራስ መኩራት ላይ አዎንታዊ ተጽእኖ ሊኖራቸው እንደሚገባ ይመክራሉ፡፡

### 4. በራስ መተማመንን ማሳደግ

ከፍተኛ በራስ መተማመንና መኩራት ለቋንቋ መማር ስኬታማነት አስፈላጊ ነገሮች እንደሆኑ የተለያዩ ሙህራን ይገልጻሉ፡፡ ከእነዚህም ኔማን(195፡5) የተማሪዎች በመጻፍ አቅማቸው መተማመን የመጻፍ አቅማቸውን በማጎልበት ረገድ ያለውን ሚና ሲገልጹ‹‹ጥሩ መጻፍ የመጻፍ እውቀትና ይህንን እውቀት የምንለማመድበትን በራስ መተማመንን ይፈልጋል፡፡ ስለሆነም ጽሁፌ አያምርም ብለው ስኬታማ ጸሐፊ አይሆኑም፡፡ በተቃራኒው ጽሁፌ ያምራል ብለው ያመኑት ደግሞ ጥሩ ጸሐፊ ይሆናሉ፡፡›› በማለት ያስገነዝባሉ፡፡

ስለሆነም ‹‹የመጻፍ ማስተማሪያ ዘዴዎች በራስ መተማመን ላይ ያላቸው ተጽእኖ የተማሪዎችን ተሳትፎ በማሳደግ በመጻፍ ላይ በራስ መተማመናቸውን ሊያጎለብቱ ይገባል፡፡›› በማለት ክሪስቲሰን(1990፡146) ይገልጻሉ፡፡ ተማሪዎች ክፍል ውስጥ የሚያደርጉት ተሳትፎ በመምህራቸውና በቢጤዎቻቸው ከፍተኛ ተቀባይነትን እንዲያገኙ ስለሚያደርጋቸው በመማር ስኬታማ ስሜት እንዲሰማቸው ያደርጋል፡፡

### 2.1.3 ተማሪዎችን በመጻፍ ማጎበዝ

የመጻፍ ማስተማሪያ ዘዴዎችን አሳታፊነት፣ አስደሳችነትና ጭንቀትን ቀናሽነት ለስኬታማ ቋንቋን መማር ያላቸው አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነው፡፡ የተማሪዎችን የመጻፍ አቅምን ከማጎልበት አንጻር የሚወሰኑ ሊሆኑ እንደሚገባ ኦምሌይና ቻሞት(1990) ስላቪን (1980)ን ጠቅሰው ይገልጻሉ፡፡ ከዚህም በተመሳሰይ ሪቻርደስና ሮጀርስ(2001፡195) የመጻፍ ማስተማሪያ ዘዴዎች ጠቀሜታነትን ኤምሲገራውንቲ(1989)ን ጠቅሰው እንደሚከተለው ዘርዝረዋል፡፡

1.የሁለተኛ ቋንቋ ልምዶችን ድግግሞሽና አይነትን ይጨምራሉ፡፡

2.አዕምሯዊ እድገትን በመደገፍና የቋንቋ ክህሎትን በማመቻቸት የቋንቋ አጠቃቀምን ይጨምራሉ፡፡

3. ቋንቋን ከይዘት ተኮር መማር ጋር የማቀናጀት እድልን ይፈጥራሉ፡፡

4.የቋንቋ መነቃቃትን ለመፍጠር ከፍተኛ አይነት ያላቸውን ቁሶችን የማካተት እድልን ይፈጥራሉ፡፡

5.መምህሩ የተለያዩ ሙያዊ ክህሎቶችን እንዲካን እድል ይፈጥራሉ፡፡

6.ተማሪዎችን ቃላትን፣ ዐ.ነገርንና አንቀጽን ጥሩ አድርጎ በመጻፍ ለጥሩ ድርሰት ጸሐፊነት ያበቃሉ፡፡

### 2.1.5 የመጻፍ ትምህርት ማስተማሪያ ዘዴዎች

ዲስኤቢሊትይ ፕሮግራም ዳይሬክቶሬት (2007፡27-57)፣ ዩሐንስና ሌሎች(1994፡144) እና ሱዛን(2001፡29) እንደገለጹት ከላይ የተጠቀሱትን የመጻፍ ማስተማሪያ ዘዴዎች ንድፈሐሳቦችን መሠረት አድርገው የተፈጠሩት የመጻፍ ማስተማሪያ ዘዴዎችን ተጠቅሞ የተማሪዎችን መጻፍ ከሚያዳብሩት ዘዴዎች የሚከተሉትን ተጠቃሽ ናቸው፡፡

#### 2.1.5.1 በቁጥጥር የመጻፍ ዘዴ

ዮሐንስና ሌሎች (1994፡142) ዴቪድ ክሮስ(1991)ን ጠቅሰው ስለዚህ የመጻፍ ማስተማሪያ ዘዴ የሚከተለውን ዝርዝር አቅርበዋል፡፡ የመጻፍ ትምህርቱ ውጤት ሙሉ በሙሉ ምን እንደሚሆን በቅድሚያ የሚታወቅ ሲሆን የማስተማሪያውን ዘዴ "በቁጥጥር መጻፍን ማስተማር" እንላለን፡፡ የተጻፈን የሚገለብጡበት ወይም በቃል የተነገርን የሚጽፉበት ክንውን ለተማሪዎች ሊሠጥ ይችላል፡፡ የትምህርቱ ውጤት በቅድሚያ የሚታወቅ(የሚተነበይ) ነው ሲባል ተማሪዎች ሲገለብጡ ወይም በቃል መጻፍ ስራ ሲሰሩ ሊሳሳቱ ይችላሉ ብለን የምንችላቸውን የፊደል ቅርጾች(የሐምሳና የግእዝ፣የሳልስና የሳድስ፣ የ‹‹ፍ››፣ የ‹‹ና››፣ የ‹‹ለ››ና የ‹‹ዘ›› ድምጾች ወዘተ) ሊኖሩ እንደሚችሉ ይጠበቃል፡፡ ስለቃላት፣ ዐ.ነገሮች፣ አንቀጾች እና ስርአተ ነጥቦች ባህሪና እውቀት እንዲኖራቸውና እንዲለማመዱ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

የዚህ ማስተማሪያ በጎ ጎኑ ውጤቱ በቅድሚያ የሚታወቅ(የሚጠበቅ) በመሆኑ የተማሪዎች መልስ ልክ ወይም ስህተት መሆኑ በፍጥነት ለመንገር ወይም የእርማት ሥራ ማካሄድ

አያስቸግርም፡፡ በተጨማሪም ሁሉን ተማሪ ስለሚያሳትፍና እጃቸውን ለማፍታታትና ክሂላቸውን ለማሳደግ ጠቃሚ ነው፡፡

ደካማ ጎኑ ውጤቱ በቅድሚያ የሚታወቅ በመሆኑ የተማሪውን የግል አስተያየት አይሻም፣ያሰለቻልም፡፡ በዚህ ዘዴ ስር ሊቀርቡ የሚችሉ ክንውኖች እንደሚከተለው ተዘርዝረዋል፡፡

**ሀ.አይቶ የመገልበጥ ክንውን**

በመጻፍ ትምህርት ይህ ቀላል ስራ ሊመስል ይችላል፣ ግን ተማሪዎች አስተውለው መገልበጥ ካልቻሉ ትርጉም የሌለው ወይም ያልተፈለግ ትርጉም ሊፈጥር ይችላል፡፡ የስርአተ ነጥብ አጠቃቀምንም በዚህ ስር ማካተት ይቻላል፡፡

**ለ.የተሳሳተ ጽሁፍ ሰጥቶ ታርሞ እንዲገለበጥ ማድረግ**

ይህ ክንውን የሚሠጠው በመጻፍ ሐሳብን ለማቅረብ የሚረዱ የቃላትና የሰዋስው እውቀት እንዲኖራቸው በማሰብ ሊሆን ይችላል፡፡ በእንደ ክፍል ደረጃው ክንውኖቹ ቀላልና ጠንከር ያሉ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ለምሣሌ ‹‹አይሮፕላኖቹ በሰማይ ላይ ሲሽከረከር አየሁት፡፡›› የሚለውን ዐ.ነገር አስተካክለውና በቃላት መሀል የሚኖረውን ርቀት ጠብቀው እንዲጽፉ ብናደርግ በቁጥጥር እያስተማርናቸው ነው ያለነው፡፡

**ሐ. ክፍት (ባዶ) ቦታ ሙላ ክንውን**

ክፍት ወይም ባዶ ቦታ ሙላ ክንውን የሚባለው በአንድ ምንባብ ውስጥ ስድስት ወይም ሰባት ቃላትን እየዘለሉ ክፍት ቦታ በመተው ተማሪዎቹ ከምንባቡ ድባብ ተነስተው ክፍት ቦታዎችን እንዲያሟሉ ወይም አማራጮች ተሰጥተዋቸው ከአማራጮቹ እየመረጡ የሚያውሉበት ክንውን ነው፡፡ ቃላትንና ሰዋስውን የማስተማር አላማ ሊኖረው ሲችል እንዲሁም አሙዋልተው ሲገለብጡ የእጅ ጽህፈታቸውን በአላማ ሊያሻሽሉ ይችላሉ፡፡

**መ.በቃል መጻፍ ክንውን**

የዚህን አይነት ክንውን ተማሪዎች ከብጤዎቻቸው ወይም ከቡድን አባላት ጋር ሆነው ሊሰሩ ይችላሉ፡፡ አንዱ ተማሪ ከመማሪያ መጽሀፍ፣ ከጋዜጣ፣ ከመጽሄት፣ ከበራሪ ጽሁፎች ወዘተ ብጤውን ወይም የቡድን አባላቱን እንዲያጽፍ በማድረግ ከዚያ በስርአት መተራረምና

በመጨረሻ ጽሁፉን እያዩ አስተካክለው እንዲጽፉ ማበረታታት የመምህሩ ተግባር መመሪያ መስጠትና እየተከታተለ ማቃናት ይሆናል፡፡

**ረ.የቅነሳ ክንውን**

በአንድ አንቀጽ ወይም ምንባብ ውስጥ አስፈላጊ ያልሆኑ የቃላት ድሪቶዎችን ወይም ያለ አገባብ የተደጋገሙ ቃላትን አስወጥተው የተስተካከለውን ሐሳብ በጽሁፍ እንዲያቀርቡ ተማሪዎችን ማዘዝ ነው፡፡ የቃላትና የሰዋስው እውቀት ከማግኘታቸውም በላይ የጽህፈትን የእምቅነት ባህሪ ሊለማመዱ ይችላሉ፡፡

**2.1.5.2 ምሪት የመጻፍ ዘዴ**

ግርሀምና ሀሪስ (2001፡74-84) እንደ ገለጹት የምሪት የመጻፍ ዘዴ ሞዴላዊ የመጻፍ ዘዴ ሲባል ተማሪዎች የቋንቋ እውቀት፣ የቃላት አጠቃቀምና የተለያዩ ገጸ ጽሁፋዊ አወቃቀሮችን እንዲያውቁ ይረዳል፡፡ ዮሐንስና ሌሎች (1994፡144) ዴቪድ ክሮስ (1991)ን ጠቅሰው እንደገለጹት ይህ ዘዴ መሠረት የሚያደርገው ናሙና የሚሆን ጽሁፍ ለተማሪዎች አስተዋውቆ ተመሳሳይ የጽሁፍ ስራ እንዲሰሩ ማድረግ ነው፡፡ ምክንያቱ ተማሪዎች ናሙናዎችን እያዩ የራሳቸውን የሐሳብ ገጠመኝ በራሳቸው አባባል የሚገልጹበት ስለሆነ ነው፡፡ ትኩረቱ በድርሰት አይነት፣ በሐሳብ አደረጃጀት፣ በሐሳብ መሰናሰል ወዘተ ላይ ሊሆን ይችላል፡፡ ለምሪት መጻፍ መነሻ የሚሆኑ ሌሎች የመጻፍ ስራዎችና የእይታ ምንባቦች ሊቀርቡ ይችላሉ፡፡ የምሪት ጽሑፍ ስልታዊ ክንውኖቹም እንደሚከተለው ተዘርዝረዋል፡፡

**ሀ.ማጠቃላያ የመስጠት ክንውን**

አንድ የጽሁፍ ምንባብ አንብበንላቸው ወይም ራሳቸው አንብበው የተረዱትን ጠቅለል አድርገው በራሳቸው አባባል እንዲያቀርቡ መጠየቅ፡፡ ፍሬ ነገርና የሐሳብ ቅደም ተከተል እንዲጠበቅ ስለቃላት አመራረጥ፣ የዐ.ነገር አሰካክና የስርአተ ነጥብ አጠቃቀም ትኩረት ሊሰጥበት የሚገባው ነው፡፡

**ለ.ማስታወሻ መያዝ**

ከቋንቋ ትምህርት ውጭ በህብረተሰብ፣ በሳይንስና በስታቲክስ ትምህርት በመምህራቸው ገላጻ ሲደረግላቸው ማስታወሻ ይዘው ለቋንቋ መምህር እንዲያሳዩ ማድረግ ወይም በያዙት

የጽሁፍ ማስታወሻ ላይ ከብጤዎቻቸውና ከቡድን አባላት ጋር የጽህፈትን ባህሪ ጠብቀው ስለመጻፋቸው እንዲወያዩ ማድረግ፡፡ በውይይታቸው መጨረሻ የጋራ ማስታወሻ እንዲያዘጋጁ ማሰራት፡፡

**ሐ.ለደብዳቤ መልስ የመጻፍ ክንውን**

አንድ የደብዳቤ ናሙና ለተማሪዎች አቅርቦ ምናባዊ የሆነ መልስ እንዲጽፉ መድረግ፡፡ የደብዳቤ ቅጽን፣የቃላት አመራረጥን፣ የሐሳብ አደረጃጀትን ወዘተ በበተመለከተ ክትትል ማድረግና ማቃኛ መስጠት ከመምህሩ ይጠበቃል፡፡

**መ.ጅምር ሐሳብ የማስጨረስ ተግባር**

አንድ ጅምር ዐ.ነገር ወይም አንቀጽ ሰጥቶ ተማሪዎች ጅምሩን ሐሳብ መሠረት በማድረግ ከራሳቸው ሐሳብ አፍልቀው እንዲጨርሱ መጠየቅ ነው፡፡ አላማውም ጅምሩን ሲጨርሱ የጽህፈትን ስርአት ጠብቀው መጻፋቸውን ለማየትና ጥሩ ከሰሩ ለማበረታታት፤ችግር ካለባቸው ለማስተካከል ነው፡፡

**ሠ.የዕለት ተእለት መዝገብ የመያዝ ክንውን** (diary)

ተማሪዎች በእለት ተእለት ያጋጠማቸው ዋና ዋና ነገር መዝግበው እንዲይዙና የወሩን ወይም የሴሚስተሩን ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያቀርቡ በማድረግ ጥሩ የጽህፈት ልምድ እንዲያዳብሩ ልንረዳቸው እንችላለን፡፡ ይህ ባህል በሀገራችን ያልተለመደ ቢሆንም ማለማመዱ ተገቢ ነው፡፡ የጽሁፍ ስርአት ጠብቀው መጻፋቸውን መከታተል ሊዘነጋ አይገባም፡፡

**ረ.ካርታዎችን፣ ግራፎችንና የስታቲካዊ ዳታዎችን በጽሁፍ ተንትኖ የማቅረብ ክንውኖች**

ለምሣሌ ኤድስ በኢትዩጵያ ከተከሰተ ጀምሮ በየአመቱ የኤድስ ህሙማንና የሙዋቾችንም ቁጥር የሚያሳይ ሰንጠረዥ በማቅረብ የመጪዎቹን አመታት ክስተት እያሰቡ የግል አስተያየታቸውን እንዲያቀርቡ፣ እንዲወያዩበትና በጋራ የሚስማሙበተን አቀናጅተው እንዲጽፉ ብናደርግ የጽህፈትን ክሂል ማዳበር ይሆናል፡፡

### 2.1.5.3 ነጻ የመጻፍ ዘዴ

እንደግርሀምና ሀሪስ(2001፡74-84) ተማሪዎች አይነታዊ ጽሁፎችን በማካተት የጽህፈት ክሂል ብቃታቸውን እንዲያሳዩ እድል የሚሰጥ የጽህፈት ስልት ነው፡፡ እንደሱዛን(2001፡29) ይህ የአጻጻፍ ስልት በወረቀት ከራስ በራስ እንደሚደረግ ቃለ ምልልስ ነው በማለት ይገልጻሉ፡፡ ምክንያቱም በነጻ ጽህፈት ተማሪዎች ስለርእሱ ብቻ በማሰብ ማንኛውንም ነገር መጻፍ ይጠበቅባቸዋል፡፡ቢያንስ ለተወሰኑ ደቂቃዎች ምንም ማቆሚያ በሌለው ሁኔታ ይጽፋሉ፡፡ ስለምንም ነገር ሳይጨነቁና በመሀሉም ሐሳብ ሳይገባቸው፤ እናም ስለትክክለኛ ሰዋስው፣ የቃላት ትክክለኛ ፊደል አጣጣል ሳይጨነቁ በቃ መጻፍ ብቻ ነው የሚጠበቅባቸው፡፡ እንደ ዩሐንስና ሌሎች(1994፡144) የመምህሩ ተግባር ተማሪዎች የጻፉትን ጽሁፍ ከብጤዎቻቸው ጋር በመሆን ወይም በቡድን እየተወያዩ ርዕሱ የጠበበ መሆኑን፤ የሐሳብ አደረጃጀቱን፣ የቋንቋ አጠቃቀሙን፣ የቃላት አጠቃቀሙን፣ የስርአተ ነጥብ አጠቃቀሙን…እያነሱ እንዲወያዩ በማድረግ በችገራቸው(ባልተስማሙበት ነገር ላይ) ምክሩንና እገዛውን የሚጠይቁበትን ሁኔታ ማመቻቸት ይሆናል፡፡ በዚህም ትምህርቱን በተማሪው የተማከለ ማድረግ ይቻላል፡፡ይሁንና እንደሌሎቹ የጽህፈት ማስተማሪያ ስልቶች ዝርዝር ክንውኖች አልተቀመጡለትም፡፡

### 2.1.5.4 ሒደታዊ የመጻፍ ዘዴ

ሰለሞን ዮሐንስና ሌሎች (1994፡145) ዶናልድ ሙሬይ(1982)ን ጠቅሰው እንደገለጹት ሂደታዊ የአጻጻፍ ዘዴ በሦስት ደረጃዎች ውስጥ እንደሚያልፍ ያመለክታል፡፡ ብዙዎች ጸሐፊዎች የሚጠቀሙበት የአጻጻፍ ዘዴ ነው፡፡ የታሰበበት የመጻፍ ስራ ወደኃላ ተመልሶ ሳይታይ እንደተጀመረ ቀጥሎ አንድ ቦታ ሲደርስ የሚያበቃ አይደለም፡፡ የጻፍነው ጽሁፍ ወደተደራሲ ከመድረሱ በፊት መላልሰን የምንመለከተው መሆን አለበት፡፡ ሂደታዊ ጽሁፉን ተግባር ለተማሪዎች ማስተዋወቅንና ማለማመድን ብሎም መከታተልንና ማቃናትን ይመለከታል፡፡ በዚህ የማስተማር ዘዴ ተማሪዎች የጽሁፍ ስራቸውን ከላይ እንደተጠቀሰው በሦስት ደረጃዎች ውስጥ እንዲያሳልፉ ይጠበቃል፡፡ እነዚህም እንሚከተለው ተዘርዝረዋል፡፡

### ሀ.የቅድመ መጻፍ ደረጃ

በዚህ ደረጃ ርዕስ የሚመረጥበት፣ የሚጠብበት እና ሐሳብ ከሰው፣ ከመጻህፍትና ከራስ የሚሰበሰብበትና የሚፈልቅበት ነው፡፡ የተሰበሰበውም ሐሳብ በቅደም ተከተል የሚደራጅበት ነው፡፡ ይህ ደረጃ ስለርዕሱ ስለሚጻፍበት አላማ (ለመንገር፣ ለማግባባት፣ ለማስደሰት፣ ሰዋስዋዊ ልምድ ለማካፈል/ ስለተደራሲው .......ጸሐፊው የሚያሰላስልበት ነው፡፡

### ለ.የመጻፍ ደረጃ

ነጻ የሆነ የመጻፍ ደረጃ ነው፡፡ በቅድመ ጽህፈት ደረጃ ጸሀፊው ያሰላሰለበትን ነገር መሠረት አድርጎ በቅደም ተከተል ያደራጀውን ሐሳብ የሚጽፍበት ነው፡፡ በዚህ ደረጃ ስለሐሳብ ትክክለኛነት፣ ስለስርአተ ነጥብ፣ ስለዐ.ነገር፣ ስለቃላት፣ አንቀጽ....ዝርዝር ነገሮች ትኩረት የሚደረግበት አይደለም፡፡ በአስተዋጽኦ እየተመሩ ዝም ብሎ የሚጻፍበት ነው፡፡ ምክንያቱም እነዚህን ነገሮች ጸሀፊው ለወደፊት ሊያስተካክላቸው ስለሚችል ነው፡፡

### ሐ.ድህረ መጻፍ ደረጃ

ይህ ደረጃ በመጻፍ ደረጃ የተጻፈውን ጽሁፍ ጸሀፊው ተመልሶ የሚመረምርበትና የሚያስተካክልበት ነው፡፡ ስርዝ ድልዝ መጫት.... ይኖራል፡፡

በድህረ መጻፍ ደረጃ ጸሀፊው ስለጽሁፉ ይዘት የሐሳብ አደረጃጀት፣ ስለቃላት፣ ዐ.ነገር፣ አንቀጽ፣ ስርአተ ነጥብ፣ ስለተደራሲው የጽህፈት ባህሪ እያሰበ የሚጽፍበት ይሆናል፡፡ ጸሀፊው በዚህ የጽህፈት ደረጃ ላይ እያለ ወደቅድመ ጽህፈትና የጽህፈት ደረጃ እየተመለከተ እንደገና ደግሞ ወደ ደረሰበሰት ጽህፈት ደረጃ እየሄደ ይጽፋል፡፡ የአጻጻፉን ስልት ሂደታዊ የሚያሰኘውም ይኸው ወደኋላና ወደፊት እያሉ መጻፍ ነው፡፡ በዚህ የአጻጻፍ ስልት ወደፊትና ወደ ኋላ እየተባለ ሲሰራ ሐሳብ እንዴት ግልጽ ሊሆንና ሊጠራ እንደሚችል ዮሐንስና ሌሎች (1994፡146) ዶናልድ ሙሬይ(1982)ን ጠቅሰው በሚከተለው ስዕላዊ መግለጫ ገልጸዋል፡፡

| አንደኛ ረቂቅ | ሁለተኛ ረቂቅ | ሦስተኛ ረቂ | አራተኛ ረቂቅ |
|---|---|---|---|
| አሰበ(exploration) | | | ግልጸት(clasification |
| ማሰላሰል<br>ማርቀቅ<br>መከለስ | ማሰላሰል<br>ማርቀቅ<br>መከለስ | ማሰላሰል<br>ማርቀቅ<br>መከለስ | ማሰላሰል<br>ማርቀቅ<br>መከለስ |

ማሰላሰል ቅድመጽህፈት ደረጃን፣ ማርቀቅ የጽህፈት ደረጃን፣ መከለስ ድህረ ጽህፈት ደረጃን ይወክላል፡፡ እንግዲህ በሂደታዊ የአጻጻፍ ስልት የሚጠቀም ሰው በእነዚህ ሦስት ደረጃዎች በኩል ሲጽፍ የጽሁፉ ሥራ አበቃለት ማለት አይደለም፡፡ በስዕላዊ መግለጫው ውስጥ እንደምንመለከተው በእነዚህ ሦስት ደረጃዎች ውስጥ ሲያልፍ ጸሀፊው አንደኛ ረቂቅ ነው የሰራው፡፡ ከአንደኛው ረቂቅ ዝቅ ብለን ስዕሉን ብንመለከት የታሰበው ሐሳብ ብዙ ነው፡፡ ከመብዛቱም የተነሳ የሐሳብ መጨናነቅ አለና ግልጸት የሚለውን ክፍል ስናይ ትንሽ ነው፡፡ አላማችን ደግሞ ሐሳብ ግልጽ እንዲሆን ነው፡፡ስለዚህ ሁለተኛውን፣ ሦስተኛውን፣ አራተኛውንና ሌሎች ረቂቆችንም ከስዕላዊ መግለጫው እንደሚታየው ደጋግመን፣ ጨምረን የራሳችንን ስራ ስንሠራ የሚታሰሰው ነገር እያነሰ(አራተኛው ረቂቅ ላይ ያለውን ስፍራ ተመልከት) የሐሳብ ግልጽነቱ እየሰፋ ይሄዳል፡፡

ከልምድ እንደሚታየው ተማሪዎች የመጻፍ ስራቸውን ለመምህሩ የሚሰጡት በአንደኛ ረቂቅ ደረጃ ላይ እያለ ነው፡፡ የሂደታዊ ዘዴ ስልት የሚነግረን ግን ተማሪው በግሉና ከሌሎች ጓደኞቹ ጋር ሆኖ በተለያዩ ረቂቆች ውስጥ ስራውን አሳልፎ ማቅረብ እንዲችል በማድረግ ክሂሉን እንዲያዳብር መርዳት እንደሚቻል ነው፡፡ ተማሪዎች እንደመመሪያ የሚጠቀሙበትን ነገር አዘጋጅቶ መስጠት በግልና በቡድን ሲሰሩ ይጠቅማቸዋል፡፡

### 2.1.6 የመጻፍ ትምህርት ማስተማሪያ ዘዴዎች ስልተ አተገባበር

የጽህፈት ማስተማሪያ ስልቶቹ አተገባበር ድርጊታዊ ምርምርን የተከተለ ነው፡፡ ምክንያቱም እንደ ሆፐኪንስ (1993:45) የጽህፈት ማስተማሪያ ስልቶቹ ስልታዊ አተገባበር ከተማሪዎቹ የጽህፈት ክሂል ውጤት አንጻር የሚመዘን በመሆኑ በተቀናጀ የክፍል ውስጥ አተገባበር ሊከናወን ችሏል፡፡ በመሆኑም እያንዳዳቸው ለደረጃቸው የሚመጥኑ ግኑኙነት ያላቸውን ዙሮች ቅደምተከተላዊ ትግበራዎችን በሚከተለው መንገድ ተከንውነዋል፡፡

**ሀ.ማቀድ**

ስልታዊ አተገባበሩ ሲታቀድ የሚከተሉት ነጥቦች ተካትተዋል፡፡

**አንድ**

I. ቁሶችን(ሞዴል ጽሁፎችን)ማዘጋጀት
II. እቅድ ማዘጋጀት
III. የድርጊቱን አፈጻጸማዊ ደረጃዎችን መንደፍ

**ሁለት**

የተማሪዎችን ነጥብ መያገ ከነስማቸው ማዘጋጀት

**ሦስት**

የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን ማዘጋጀት

**አራት**

የክፍል ውስጥ ምልከታ ማመሳከሪያ ቅጽ ማዘጋጀት

**አምስት**

ፈተና ማዘጋጀት፡፡

**ስድስት**

እንደ ዴላ ፓዝና ግርሐም (1997፡174)እያንዳንዱ የጥናቱ ተሳታፊ ከ45-50 ደቂቃ በትምህርት ቤት ውስጥ ከ4-8 ክፍለ ጊዜ ባላነሰ ሁኔታ በዘዴዎቹ ይማራሉ፡፡ በዚህም ጥናት አራቱም የመጻፍ ማስተማሪያ ዘዴዎች አምስት አምስት ክንውን ሰላላቸው የእያንዳንዱ ዘዴ የጥናት ተሳታፊዎች ለአምስት ቀን በዘዴዎቹ ለ50 ደቂቃ ያህል ተምረዋል፡፡

**ለ.ድርጊት**

1. በዘዴዎቹ ማስተማር
2. ምልከታ ማድረግ፡፡
3. መረጃ ትንተና፡፡
4. ውጤት ገለጻ፡፡

የዘዴዎችን አተገባበራዊ ሂደትና ድርጊት ደረጃ በደረጃ ለማካይሄድ ታቅዷል፡፡ በመሆኑም ቅደም ተከተላዊ ቅንጅቱም በሚከተለው የኡስማህንቱ ሀሰናህ (2012፡56) የመስመር ስዕል (Diagram) ሞዴል ናሙናን በማሻሻልና ከዚህ ጥናት ጋር በማጣጣም የመጻፍ ማስተማሪያ ዘዴዎቹን አተገባበራዊ ቅደም ተከተል እንደሚከተለው ተገልጸዋል፡፡

## 1.በቁጥጥር መጻፍ ዘዴ ክንውኖች





ዙር አራት
የተማሪዎች የጽህፈት ችግር
የቁጥጥር መጻፍ
ድርጊት አራት
የቃል ጽህፈት ክንውን
ምልከታ አራት
መረጃ መተንተን
ገለጻ
ዙር አምስት
የመጻፍ ችግር
የቁጥጥር መጻፍ
ድርጊት አምስት
የቅነሳ ክንውን
ምልከታ አምስት
መረጃ ትንተና
ገለጻ

## 2.የመር መጻፍ ዘዴ ክንውኖች




ዙር አራት
የተማሪዎች የመጻፍ ችግር
የምሪት መጻፍ
ድርጊት አራት
ጅምር ሐሳብ የማስጨረስ ተግባር
ምልከታ አራት
መረጃ መተንተን
ገለጻ


ዙር አምስት
የመጻፍ ችግር
የምሪት መጻፍ
ድርጊት አምስት
ስታቲስቲካዊ ግራፎችን በጽሁፍ ተንትኖ ማቅረብ
ምልከታ አምስት
መረጃ ትንተና
ገለጻ

## 3.የነጻ መጻፍ ክንውኖች




ዙር ሦስት
የመጻፍ ችግር
በነጻ መጻፍ
ድርጊት ሦስት
ረቂቅ መጻፍ
ምልከታ ሦስት
መረጃ ትንተና
መረጃ ትንተና
ዙር አራት
የተማሪዎች የመጻፍ ችግር
በነጻ መጻፍ
ድርጊት አራት
ስለሚጽፉት ርእስ ብቻ በማሰብ መጻፍ
ምልከታ አራት
መረጃ መተንተን
ገለጻ

ዙር አምስት




## 4.የሒደታዊ መጻፍ ዘዴ ክንውኖች

ዙር አንድ




ዙር ሁለት
የመጻፍ ችግር
ሒደታዊ መጻፍ
ድርጊት ሁለት
ሐሳብ መጨመር ወይም
ምልከታ ሁለት
መረጃ ትንተና
ገለጻ
ዙር ሦስት
የመጻፍ ችግር
ሒደታዊ መጻፍ
ድርጊት ሦስት
የመጻፍ ደረጃ ክንውኖች
ምልከታ ሦስት
መረጃ ትንተና
ገለጻ


ዙር አራት
የመጻፍ ችግር
ሒደታዊ መጻፍ
ድርጊት አራት
የመጀመሪያ ረቂቅ ክንውኖች
ምልከታ አራት
መረጃ ትንተና
ገለጻ
ዙር አምስት
የመጻፍ ችግር
ሒደታዊ መጻፍ
ድርጊት አምስት
ድህረ መጻፍ ደረጃ ክንውኖች
ምልከታ አምስት
መረጃ ትንተና
ገለጻ

## 2.2 የተዛማጅ ጽሁፍ ቅኝት

በዚህ አውደ ርዕስ ስር ከመጻፍ ትምህርት ማስተማሪያ ዘዴዎች ሚና ትንተና ጋር ተዛማጅነትና መነሻ ሐሳብ የሆኑት ጽሁፎች እንደሚከተለው ተቃኝተዋል፡፡

በአጠቃላይ በቁጥጥር፣ በመር፣ በነጻና በሒደታዊ የመጻፍ ማስተማሪያ ዘዴዎች መካከል አተገባበራዊ ልዩነቶች ቢኖሩም የተማሪዎችን የመጻፍ ትምህርትን በማጎልበት ረገድ አንዱ ከአንዱ መሻሉን ለመረዳት ተግባራዊ ሙከራን ይሻሉ፡፡ በቁጥጥር መጻፍ ዘዴ እንደ ዲሰቢሊይ ፕሮግራም ዳይሬክቶሬት (2007፡27-56)፣ ሰለሞን ዩሐንስና ሌሎች (1994፡143) ዴቪድ ክሮስን (1991) ጠቅሰው የትምህርቱን ውጤት በቅድሚያ የሚተነብይ ዘዴ ነው፡፡ ጥሩ ጎኑ ተማሪዎች ሊፈጽሟቸው የሚችሉት የመጻፍ ግድፈቶችን ቀድሞ ስለሚተነብይ አፋጣኝ እርማት ለመስጠትና ሁሉንም ተማሪዎችን ለማሳተፍ ያስችላል፡፡ ይሁንና የራሱ የሆነ ደካማ ጎን አለው፡፡ ይሄም ተማሪዎች የሚፈጽሟቸውን የመጻፍ ግድፈቶች ቀድመው ስለሚታወቁ የተማሪውን የግል አስታየት ስለማይፈልግ አሰልቺ ነው በማለት ይገልጻሉ፡፡

በምሪት የመጻፍ ሰለሞን ዩሐንስና ሌሎች (1994፡144) ዴቪድ (1991)ን ጠቅሰው፣ ዲሰቢሊትይ ፕሮግራም ዳይሬክቶሬት (2007፡27-56) ይህ ዘዴ ተጨማሪ እርዳታን የሚሹ ተማሪዎችን ለማገዝ እና እውቀት፣ ክሂልና መረዳት ላይ እንዲመሰረቱ ያደርጋል፡፡ በተጨማሪም ውስንና በሙሉ ክፍሉን የሚያሳትፍ ከመሆኑም በላይ መምህሩን እንደ አጋዥ በመቁጠር ስኬታማ፣ አውዳዊና አስተማሪ ቡድንን ይፈጥራል በማለት ይገልጻሉ፡፡

እንደ ዲሰቢሊትይ ፕሮግራም ዳይሬክቶሬት(2007፡27-56) በነጻ መጻፍ ዘዴ ተማሪዎች ተግባራትን ለመግለጽ፣ አንባቢያቸውን ለመለየት፣ ወደ ከፍተኛ ምርምር ለመሸጋገር፣ በፍጥነት ሐሳብን አሳጥሮ ለመጻፍ፣ ረቂቅ ለመጻፍ ይበረታታሉ፡፡ ትምህርቱም በተማሪዎች የተማከለ ያደርጋል፡፡

ሌላኛው የመጻፍ ዘዴ ሂደታዊ ሲሆን ሰለሞን ዩሐንስና ሌሎች (1994፡146) ዶናልድ (1982)ን በመጥቀስ ተማሪዎችን ብቁ ጸሐፊዎች እንደሚያደርግ እና በመጻፍ ምዘናዎች የተሻለ ውጤትን ያስመዘግባሉ በማለት የተለያዩ ጥናቶችን መሠረት አድርገው ያስረዳሉ፡፡

እንደ ጉኦ ያን (2005፡19) ዘውጋዊ የመጻፍ ማስተማሪያ ዘዴ ከ1980ዎቹ ወዲህ የመጣ ዘዴ ሲሆን ተማሪዎች የተለያዩ የጽሁፍ አይነቶችን በማጥናት የመጻፍ ክሂላቸውን

የሚያሳድጉበት ዘዴ ነው፡፡ ምክንያቱም ጽሁፎቹ በተለያዩ የሰዋስውና የመዋቅር ቅርጾች በመሞላታቸው እነዚህን በማጥናት የጽሁፍን ተግባቦታዊ ብቃትን በመረዳት የመጻፍ ክሂላቸውን እንደሚያሳድጉ ይገልጻሉ፡፡

እንደ አንቶንይ(2005፡4) እና ባድገርስ (2000)፣ ፒያጋ(1986)፣ ነኢድ(1993)ን በመጥቀስ ሒደታዊ የመጻፍ ማስተማሪያ ዘዴ ከቁጥጥር፣ መር፣ ነጻና ዘውጋዊ ጋር ሲወዳደር ለአንዳንዶች ሊዋጥ ያልቻለ የውሸት ሐሳብ ቢመስልም እጅግ በጣም አስፈላጊ ነው በማለት ይገልጻሉ፡፡ በማስከተልም አንቶንይ(2000፡4) ብሩቶን(1983)ን ዋቢ በማድረግ መጻፍ ቅይጣዊ ተግባር ነው በሚለው እሳቤ ቁጥጥር፣ መርና ነጻ በአንድ ክፍል እንደሚመደቡና ራይምስ(1976)ን በመጥቀስ ደግሞ ቁጥጥርና ነጻ ደረጃ በደረጃ ሊከናወኑ ይችላሉ በማለት ይገልጻል፡፡ በተጨማሪም ባይረን(1979)ን መሰረት በማድረግ በጊዜ ሒደት ከቁጥጥር ወደ መር፣ ከዚያም ወደ ነጻ ተግባራት ሽግግር በማድረግ ሊከናወኑ ይችላሉ በማለት ያስገነዝባሉ፡፡

እንደሂስማኖጉሉ (2005) ጥናት የቁጥጥር፣ የመርና ነጻ የመጻፍ ዘዴዎች ለሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች የመጻፍ ችሎታቸውን በማሻሻል ረገድ የተሻሉ መሆናቸውን ሲገልጽ፤ የዱፕለሲስ (2012) ጥናት ደግሞ ምሪት፣ ሂደታዊና ዘውጋዊ የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ እንዳሻሻሉ ይገልጻሉ፡፡ ይሁንና ይበልጥ ውጤታማ የሆነው ስልት ደግሞ ሒደታዊ ዘውግ እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡ እንደ ኢስማኤል(2008)ና በሊንዳ(2006) ሒደታዊ የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ ውጤታማ በማድረግ ከፍተኛ መሆኑን በጥናታቸው ያስረዳሉ፡፡ በተመሳሳይም ዚንዩ ቂያን (2010፡14) የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታን በመካከለኛ ደረጃ ለማስተማርም የሒደታዊ ዘዴ ጠቀሜታ እንዳለው ቢገልጹም ግን የተማሪዎችን የሰዋስው እውቀት እነደማያሻሽል የተለያዩ ጥናቶችን ዋቢ በማድረግ ያስረዳሉ፡፡

በዱፕለሲስ (2012) የተሠራ የሁለተኛ ድግሪ መመረቂያ ጽሁፍ ነው፡፡ ጥናቱም በናሚቢያ የእርዳታ ድርጅት ተማሪዎች የመጻፍ ክሂልን ለማሻሻል የመጻፍ ዘዴዎች ትግበራ ድርጊታዊ ምርምር ነው፡፡ ይህም ድርጊታዊ ምርምር ሦስቱን የመጻፍ ማስተማሪያ ዘዴዎችን (ሂደታዊ፣ ሞዴል እና ሂደታዊ ዘውግ(process gener) በማነጻጸር ላይ የተካሄደ ነው፡፡ አጥኚው ሦስቱንም ዘዴዎች በተናጥል በሦስት ክፍሎች በመተግበር፤ በመጠናዊና በአይነታዊ የምርምር ዘዴዎች እና በጽሁፍ መጠይቅ፣ በቅድመና ድህረ ትግበራ የድርሰት

ፈተና፣ በላብራቶሪ ሪፖርትና በቃለመጠይቅ በመታገዝ ጥናቱን እንዳከናወነ ይገልጻል፡፡ እነዚህን የምርምሩን አካሄዶች በመከተል የጥናቱ ውጤትም የሚያመለክተው ሦስቱም የመጻፍ ማስተማሪያ ዘዴዎች የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል እዳሻሻሉና ሂደታዊ ዘውግ(process gener) ዘዴ ከሁለቱ በተሻለ ሁኔታ የተማሪዎቹን የጽህፈት ክሂል በማሻሻል ረገድ ከፍተኛ ውጤትን ሊያስመዘግብ ችሏል፡፡

የዱፕለሲስ(2012) ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር የሚያዛምዳቸው ሁለቱም ጥናቶች በመጻፍ ማስተማሪያ ዘዴዎች ውጤታማነት ፍተሻ ላይ የተካሄዱ መሆናቸው ነው፡፡ ይሁንና የሚያለያዩዋቸው ነጥቦችም አሉ፡፡ የዲፕለሲስ ጥናት በሦስት የመጻፍ ማስተማሪያ ዘዴዎች ውጤታማነት ፍተሻ ላይ የተካሄደ ድርጊታዊ ምርምር ሲሆን፣ ይህ ጥናት ግን በአራት (በመር፣ ነጻ፣ ቁጥጥርና ሂደታዊ) የመጻፍ ማስተማሪያ ዘዴዎች ሚና ትንተና ላይ የተካሄደ ነው፡፡ ሌላው የሚያለያያቸው ጉዳይ የጥናቱ ተሳታፊዎች ምርጫ ላይ ነው፡፡ ይህም በዲፕለሲስ ጥናት የማስተማሪያ ዘዴዎቹን በዩኒቨርሰቲ ተማሪዎች ተተኳሪነት የተገበራቸው ሲሆን፤ በዚህ ጥናት ግን የጥናቱ ተተኳሪዎች የሁለተኛ ደረጃ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች በመሆናቸው ይለያያሉ፡፡

እንደዚሁም እነዚህ ሁለት ጥናቶች የሚስማሙበትና የማይስማሙበትም ነጥቦች አሉ፡፡ ከሚስማሙበና ከማይስማሙበት ነጥቦች አንዱ የመጻፍ ማስተማሪያ ዘዴዎችን የተመለከቱበት አቅጣጫ ነው፡፡ ይህም የዱፕለሲስ ጥናት የመጻፍ ማስተማሪያ ዘዴን የተመለከተው ከስነልሳናዊ አንድምታ አንጻር ነው፡፡ ይህ ግን የመጻፍ ማስተማሪያ ዘዴዎቹን ክሂላዊ ልምምድን አይገልጽም፡፡ ምክንያቱም አንድ የማስተማሪያ ዘዴ አዕሯዊ፣ ሜታ አዕምሯዊ፣ ስሜታዊና ማህበራዊ ርስቶችን ማሳካት ይጠበቅበታል፡፡ በዱፕለሲስ ጥናት ግን ይህ ጉዳይ አልታየም፡፡ በሱ ጥናት የታየው የተማሪዎች መጻፍን ከይዘታዊ ሽፋን አንጻር ነው፡፡ በእርግጥ ጥናቱ በዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ተሳታፊነት የተሰራ በመሆኑ በመዋቅራውያንና በባህራውያን ንድፈ ሐሳብ የተደገፈ ቢሆንም የመጻፍ ማስተማሪያ ዘዴዎቹን ክሂላዊ ማለማመጃነትን የተሟላ አያደርገውም፡፡

በዚህ ጥናት ግን ከሞላ ጎደል የመጻፍ ማስተማሪያ ዘዴዎቹ ክሂላዊ ልምምዶች የተሟሉ እንዲሆኑ አስችሏል፡፡ ይህም በተወሰነ መልኩ ከአሳታፊነት፣ መጻፍን አስደሳች ተግባር ከማድረጋቸው፣ ጭንቀትን ከመቀነሳቸውና በመጻፍ ከማጎበዛቸው አንጻር ለመተንተን ተሞክሯል፡፡ በዚህም የተለያዩ ርስቶችን(Domains) ለማካተት ተሞክሯል፡፡

በተሬዛ (1998) ለድህረ ምረቃ የተሰራ ምርምር ነው፡፡ ይህም በስርአተ ትምህርት ውስጥ መጻፍንና ሒደታዊ ዘዴን ተጠቅሞ መጻፍን በማስተማር የመጻፍ ችግር ያለባቸውን ተማሪዎችን ማሻሻል ነው፡፡ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎቹም የተማሪዎች ድህረና ቅድመ ፈተናዎች እና የመምህሩ ምልከታዎች ናቸው፡፡ በፈተና የተገኘው ውጤት የተማሪዎቹ የመጻፍ ክሂል መሻሻሉን ባያሳይም፤ በምልከታ የተሰበሰበው መረጃ ውጤት ግን በተለያዩ የትምህርት ዘርፎች የተማሪዎቹ መጻፍ እንደተሻሻ ይገልጻል፡፡

ይህ ጥናት ከተሬዛ ጋር የሚያዛምደው ሁለቱም ጥናቶች የመጻፍ ማስተማሪያ ዘዴዎች ሚና ናቸው፡፡ ይሁንና የተሬዛ ጥናት መጻፍንና ሒደታዊ የመጻፍ ማስተማሪያ ዘዴን በተለያዩ የትመህርት ዘርፎች ውስጥ በመጠቀም የደካማ ተማሪዎችን መጻፍ በማሻሻል ረገድ ያላቸውን ሚና ተንትኗል፡፡ ይሁንና ከዚህ ጥናት ጋር የማይስማበት ነጥብም አለ፡፡ ይህም በትሬዛ ጥናት በየትኛው ንድፈ ሐሳብ እንደተቃኘ ግልጽ ብሎ የተቀመጠ ነገር የለም፡፡ ሁንና የማስተማሪያ ዘዴውን ሚና የተመለከተው ከስነልሳዊ ይዘት ብቻ ነው፡፡ በቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴዎች ስነልሳናዊ ግብ አንዱ ቢሆንም በተለይም የሁለተኛ ቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴዎች ስነልሳናዊ ግብ ሊጎለብት የሚችለው ከሌሎች ርስቶች አጋዥነት ጭምር ነው፡፡ በመሆኑም በዱፕለፐሲስ ጥናት የፈተናም ሆኑ የምልከታ መረጃዎች ተመሳሳይ ናቸው፡፡ ይህም የማስተማሪያ ዘዴዎቹን ሚና ከመጻፍ ስነልሳናዊ ለውጥ አንጻር ነው የተመለከቱት፡፡ በዚህ ጥናት የመጻፍ ማስተማሪያ ዘዴዎችን የአሳታፊነት፣ መጻፍን አስደሳች ተግባር ከማድረግ አንጻር፣ ተማሪዎችን በመጻፍ ከማጎበዝ አንጻርና መጻፍ ከሚያከብዱ አንዱ ከሆነው ጭንቀትን ከመቀነሳቸው አንጻር ያላቸውን ሚና ለመተንተን ተሞክሯል፡፡

በሳራፐና ሰፊክ (2008) የተሰራ በሂደታዊ የመጻፍ ማስተማር ዘዴ የድርሰት ክሂልን ማስተማር ድርጊታዊ ምርምር ነው፡፡ አላማውም ሂደታዊ መጻፍን ማስተማር ዘዴ የተማሪዎችን የድርሰት ክሂልን በማሻሻል ረገድ ያለውን ሚና መመርመር ነው፡፡ መረጃዎችም በቪዲዮ ቅጅዎች፣ ገለጻዊ ማስታወሻዎች፣ የመምህሩ ማስታወሻዎች እና ድረሰታዊ ፈተናዎች የተሰበሰቡ ናቸው፡፡ በአይነታዊና በመጠናዊ ዘዴ የተተነተኑ ሲሆን ግኝቱም የሚያመለክተው የተማሪዎች የመጻፍ ክሂል እንደተሻሻለ ነው፡፡ ይህ ጥናት ግን የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎቹ ተከታታይ ምልከታ ምልከታ ሲሆን የተሰበሰቡት መረጃዎችም በአይነታዊ ስልት ተተንትነዋል፡፡ አተገባበሩም የመጻፍ ማስተማሪያ ዘዴዎችን ሚና መተንተን ነው፡፡

ይህም ጥናት ሒደታዊ የመጻፍ ማስተማሪያ ዘዴን ከስነልሳናዊ ይዘቱ ያለውን ሚና ብቻ የተነተነ ነው፡፡ ይህ ብቻውን ደግሞ የአንድ መጻፍን ማስተማሪያ ዘዴ ሚና ሊሆን አየረገባም፡፡ ምክንያም አንድ የማስተማሪያ ዘዴ ዕመምሯዊ፣ ሜታ አዕምሯዊ፣ ስሜታዊና ማህበራዊ ርስቶችን አጣምሮ ሊተውን ይገባል፡፡ ይህ ካልሆነ ስኬታማነቱን ለማረጋገጥ ሊያዳግት ይችላል፡፡ በዚህ ጥናት ግን የመጻፍ ማስተማሪያ ዘዴዎቹን ሚና ከአሳታፊነታቸው፣ ከማኅበዛቸው፣ አስደሳች ተግባር ከማድረጋቸውና ጭንቀትን ከመቀነሳቸው አንጻር ሚናቸውን ለመተንተን ተሞክሯል፡፡ እንዲሁም ይህ የሳራፕና ሰፊክስ ጥናት የመጻፍ ማስተማሪያ ዘዴዎቹን ሚና በንድፈ ሐሳብ ላይ አስደግፎ የገለጸ ባለመሆኑ ጥናቱ የመጻፍ ማስተማሪያ ዘዴዎችን ሚና ያየበት መንገድ ጉድለት ይታይበታል፡፡

በቢሊንዳ(2006) በሆንግ ኮንግ የመጀመሪያ ደረጃ ተማሪዎች ተተኳሪነት የተሰራ የሒደታዊ መጻፍን ማስተማሪያ ዘዴ ውጤታማነት ፍተሻ ላይ የተሰራ ጥናት ነው፡፡ መረጃዎችም በቃለመጠይቅ፣ በምልከታና በፈተና አማካኝነት ተሰብስበዋል፡፡ ውጤቱም የሚያመለክተው መጻፍን በሒደታዊ ዘዴ ማስተማር ውጤታማ እንደሚያደርግ ነው፡፡

የቢሊነዳ ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር የሚያመሳስለውም በመጻፍ ማስተማሪያ ስዘዴዎች ሚና ላይ ማተኮራቸው ነው፡፡ የሚያለያያቸውም ጉዳይ በቢሊንዳ አንድ የመጻፍ ማስተማሪያ ዘዴ ሚና ሲፈተሽ በዚህ ጥናት ግን አራት ማስተማሪያ ዘዴዎች ሚና ተተንትኗል፡፡ ምክንያቱም እንደ ሐገራችን አውድ አራቱንም የመጻፍ ማስተማሪያ ዘዴዎች የመጠቀሙ ጉዳይ የተለመደ በመሆኑ የትኛው ዘዴ ለተማሪዎች መጻፍ ምቹ ሁኔታዎችን በመፍጠር ከፍተኛ ሚና ይጫወታል የሚለውን በመተንተን ላይ ስለሚያተኩር ነው፡፡ ሌላው የማያስማማቸው ጉዳይ የየመጻፍ ማስተማሪያ ዘዴዎችን ሚና የሚያዩበት መነጽር ነው፡፡ ይህም በቢሊንዳ ጥናት ሒደታዊ የመጻፍ ፣ስተማሪያ ዘዴዎችን ያየበት ንድፈ ሐሳባዊ መነጽሮች መዋቅራውያንና ባህራውያን ይሁኑ ወይም አዕምሯዊያንና ሌሎች መሆናቸውን ግልጽ ያለ ነገር የተቀመጠ የለም፡፡

በቶማስ(2007) ለዶክተሬት ድግሪ ማሟያነት በሒደታዊ ዘውግና በምሪት መጻፍ ማስተማሪያ ዘዴ ውጤታማነት ፍተሻ ላይ የተሰራ ጥናት ነው፡፡ የጥናቱም ተተኳሪዎች የማይለገፒያ ሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ናቸው፡፡ መረጃዎችም በፈተናና በቃለ መጠይቅ ተሰብስበዋል፡፡ ውጤቱም የሚያመለክተው በምሪት ከተማሩት ተማሪዎች ይልቅ በሒደታዊ

ዘውግ የተማሩት ሐሳባቸውን በበቂ ሁኔታ በማብራራት ለአንባቢው ማቅረብ እንደቻሉ ያመለክታል፡፡

የቶማስ ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው ሁለቱም የመጻፍ ማስተማሪያ ዘዴዎችን ሚና መተንተን ላይ የሚያተኩሩ ናቸው፡፡ ይሁንና ሁለቱም የሚያለያዩዋቸው ነገሮች እንዳሉም ይታያል፡፡ የመጀመሪያው የሚያለያያቸው ጉዳይ ቶማስ(2000) ሒደታዊ ዘውግና ምሪትን ሲያነጻጽር፤ በዚህ ጥናት ግን ቁጥጥር፣ መር፣ ነጻና ሒደታዊ ዘዴዎች መጻፍን በማስተማር ረገድ ያላቸውን ሚና መተንተን ላይ ያተኮረ ነው፡፡ ሌላው የሚያለያያቸው ጉዳይ በቶማስ ጥናት ቃለመጠይቅና ፈተና ለመረጃ መሰብሰቢያነት ሲያገለግሉ፣ በዚህ ጥናት ግን ተከታታይ ምልከታ በመረጃ መሰብሰቢያነት አገልግሏል፡፡ የመጻፍ ማስተማሪያ ዘዴዎቹን ሚና የተመለከተበት አይን ለክሂላ ልምምዱ በቂ አይመስልም፡፡ ምክንያቱም የመጻፍ ማስተማሪያ ዘዴዎች ሚና ከአሳታፊነታቸው፣ መጻፍን አስደሳች ተግባር ከማድረጋቸው፣ ተማሪዎችን በመጻፍ ከማነሳሳታቸውና ጭንቀትን ከመቀነሳቸው አንጻር እንደማንኛውም የዘመኑ ስኬታማ የቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴ ሁሉ ሙሉ ሚናቸውን ሊወጡ ይገባል፡፡

## ምዕራፍ ሦስት

## የምርምሩ ዘዴ

### 3.1 የጥናቱ ዘዴ

የመምህራን ሆነ የተመራማሪዎች ትልቁ ግብ ስኬታማ የማስተማር ዘዴ የትኛው ነው የሚለውን ማወቅ ነው፡፡ ይህም ግብ በትክክል በመጀመሪያ የመጻፍ ማስተማሪያ ዘዴዎች መጻፍን ለማስተማር እንዴት ምቹ እንደሆኑ ለመለየት ቀደምት እወቀት ያስፈልጋል፡፡ የእዚህ መሠረታዊ እውቀት ትክክለኛነት ደግሞ የሚመሰረተው በተለያዩ የማጻፍ ማስተማሪያ ዘዴዎች መቼት ነው፡፡ ይህ ጥናትም የተበየነው በሁለት ተዛማጅ ተግባራት ነው፡፡ አንደኛው በተወሰኑ ወካይ መቼቶች ትክክለኛና ጠቃሚ የመጻፍ ማስተማሪያ ዘዴዎች ክንውን በማድረግ ነው፡፡ ሁለተኛው ደግሞ እነዚህን ክንውኖች በሌሎች ብዙ መቼቶች እንዲለመዱ ማድረግ ነው፡፡ ይሁንና የመጻፍ ማስተማሪያ ዘዴዎች ክንውኖች የተለያየ ውጤት ቢያሳዩም ለሌሎች ንጽጽራዊ ጥናቶች መነሻ ይሆናል፡፡ ምንም አይት የመጻፍ ትምህርት ለብቻው በማይሰጥበትና በትምህርት ቤቱ ለአጠቃላይ ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሳምንት አንድ ክፍል ጊዜ ብቻ የተሰጠው በመሆኑ ጥናቱ ገላጭ መሆኑ አስፈልጓል፡፡

ጥናቱን ለማካሄድ ሁለት ውሳኔዎች ደርገዋል፡፡ የመጀመሪያው የመጻፍ ትምህርት ለብቻው በማይሰጥበት ሁኔትና የተመደበው የቋንቋ ትምህርት ክፍለጊዜን ከግምት ውስጥ በማስገባት የመጸሸፍ ማስተማሪያ ዘዴዎቹን የተወሰኑ ክንወኖች እንዲዘጋጁ በማድረግ በናሙና በተመረጡ ተማሪዎች ላይ እንዲተገበሩ ተደርጓል፡፡በዚህ ላይ በመመስረት የመጻፍ ማስተማሪያ ዘዴዎቹን ውጤት ለመለየት ተሞክሯል፡፡ ሁለተኛው ውሳኔ በየትኛው መለኪያ ቢነደፍ ነው ድምዳሜ ላይ መድረስ የሚቻለው? የሚለው ነው፡፡ ይህንን ለመወሰን ገላጭ የምልከታ ሞዴል ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ ይህም ዘዴዎቹ የተማሪዎችን መጻፍ ከማጎልበተር አንጻር ያላቸውን ሚናን ለመለካት አስችሏል፡፡  በተጨማሪም የመምህሩን ሚናን አካቶ ይዟል፡፡ ምክንያቱም መምህሩ የመጻፍ ማስተማሪያ ዘዴዎቹ ብቸኛው መሪ በመሆኑ ነው፡፡ ጠቀሜታውም ዘዴዎቹ በትክክለኛው አካሄድ መቅረባቸውን ለማረጋገጥ ስለሚያስችሉ ነው፡፡

### 3.2 የጥናቱ ተሳታፊዎች

ይህ ጥናት ተሳታፊ ያደረገው ኦሮመኛ አፊ ፊት 9ኛ ክፍል ተማሪዎችን ነው፡፡ የጥናቱ ተሳታፊዎች በኦሮሚያ ክልል፣ በጅማ ዞን፣ በሊሙ ኮሳ ወረዳ፣ በአምቡዬ ከተማ በሚገኘው በአምቡዬ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት 9ኛ ክፍል ኦሮመኛ አፍ ፊት የ2009 ተማሪዎች ተተኳሪነት ተካሂዷል፡፡ በቅድመ ጥናት በተደረገው ማጣራት መሰረት በ2009 ተመዝግበው እየተማሩ ያሉት ተማሪዎች ብዛት 589 እንደሆነ ከትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር የተገኘው መረጃ ያመለክታል፡፡ በተደረገው የአሰሳ ጥናትም 228ቱ አማርኛ አፍ ፊት ሲሆኑ 361 ደግሞ ኦሮመኛ አፍ ፊት ናቸው፡፡ ከ361 ኦሮመኛ አፍ ፊት ከሆኑት 9ኛ ክፍል ተማሪዎች ውስጥ በቀላል የእጣ ናሙና 118 ተማሪዎች በቅድመ ድርሰት ጻፍ ፈተና ላይ እንዲሳተፉ ተደርጓል፡፡ በቅድመ ፈተና ከተሳተፉት ውስጥም የተማሪውን የመማር ጥረት፣ የጾታ ስብጥርና አፈንጋጭ ነጥቦችን ከግምት ውስጥ በማስገባት በተደረገው የማጣራት ስራ 24 ተማሪዎች በጥናቱ እንዲሳተፉ ሆኗል፡፡ እነዚህም 12 ወንድና 12 ሴት ተሳታፊዎችን ያቀፈ ነው፡፡ ጥናቱ እነዚህ ተማሪዎች ላይ ተተኳሪ በማድረግ እንዲከናወን የተደረገበት ምክንያት እንደ ዞውሬዝ (2010፡25) ስኩነን(2003)ን ጠቅሳ እንደገለጸችው ጽህፈት ከአፈፈት ይልቅ የኢ አፈፈቱን ከፍተኛ አቅምን ስለሚፈልግ ነው፡፡

የተመረጡት ተማሪዎች በቀላል እጣ ናሙና አማካኝነት ቁጥጥር፣ መር ነጻና ሒደታዊ የጽህፈት ማስተማሪያ ስልቶች ስድስት ስድስት ተማሪዎችን እንዲሳተፉ ተደርጓል፡፡ አራቱም ስልቶች ሦስት ወንድና ሦስት ሴት ተማሪዎችን አሳትፈዋል፡፡

በዚህ ጥናት የተሳታፊዎችን ቁጥር ለመወሰን የተገደደው ጥናቱ በአይነቱ ተግባራዊ ሙከራን የሚፈልግ በመሆኑ ነው፡፡ ይህንን የናሙና አመራረጥ ዴላ ፓዝና ግርሀም (1997፡169)፣ ግርሐምና ሐሪስ (1989)፣ ያለው(2006፡142) ይደግፉታል፡፡ ምክንያቱም የጽህፈት ትምህርት ለብቻው በማይሰጥበት ሁኔታ የመጻፍ ማስተማሪያ ዘዴዎችን ውጤታማነት መፈተሹ ስለሚያዳግት ነው፡፡

### 3.3 የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ

